# የሐዋርያት ሥራ

## ትምህርት ሁለት

### ውቅርና ይዘት

## The Book Of Acts

### Lesson Two

### Structure and Content

## ተርጓሚ፡እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓት-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓት-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

## አስተዋፅዖ


1. **መግቢያ**
2. **የአጻጻፍ ስልት**

    ግልፅ ዓላማ

        ታሪካዊ መረጃ

        የወንጌል መልእክት

    በሥልጣን መደገፍ

        ቃላት

        ሥራዎች

    የአወቃቀር ንድፍ

        ጥቅል ዐረፍተ-ነገር

    የቤተክርስቲያን እድገት

3. **ይዘት**

    ኢየሩሳሌም

    ይሁዳና ሰማርያ

    የምድር ዳር

        ፊንቄ፣ ቆጵሮስ እና አንጾኪያ

        ቆጵሮስ፣ ጲርጊያ እና ገላትያ

        እስያ፣ መቄዶኒያ እና አካይያ

        ሮም

4. **በእኛ ዘመን የሚኖረው ተዛምዶ**

    ስነ-ጽሁፋዊ ባህርይ

        ጠንቃቃ አመራረጥ/የተመጠነ

        አጫጭር ትረካ

        ዘወርተኛ

    የተቋረጡ

        የተለያየ ጊዜ

        የተለያየ ሁኔታ

    የቀጠሉ

        ተመሳሳይ አምላክ

        ተመሳሳይ ግብ

        ተመሳሳይ ወንጌል

5. **ማጠቃለያ**

# 1. መግቢያ

እንደ አስተማሪ፣ በመላው ዓለም በበርካታ አገሮች የመጓዝ ዕድል ያጋጥመኛል፡፡ ከእያንዳንዱ ጉዞ በፊት፣ ሁለት ወሳኝ ነገሮችን በትክክል የተረዳሁ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡ በመጀመሪያ፣ ወደየት እንደምሄድ ማወቅ፡፡ ሁለተኛ፣ ከቦታ ወደ ቦታ እንዴት መዘዋወር እንደምችል፡፡ በአውሮፕላን እበራለሁ? አውቶቡስ እሳፈራለሁ? ወይስ ሌላ ዓይነት ትራንስፖርት እጠቀማለሁ? የሚሉትን ማወቅ ይገባኛል፡፡ የሐዋርያት ሥራን ስናነብብም ተመሳሳይ የሆነ እውነት አለ፡፡ ታሪኩ ወደየት እንደሚያመራ ማወቅና እና ሉቃስ ወደ መዳረሻው የሚያደርሰን ምን አይነት ስነ-ጽሁፋዊ ዘዴዎችን ወይም ስልቶችን ተጠቅሞ ነው የሚለውን ማወቅ አለብን፡፡

የሐዋርያት ሥራ ከተሰኘው ተከታታይ ጥናታችን ይህ ሁለተኛው ነው፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርት፣ የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን በኢየሱስ የተጀመረውን አገልግሎት የቀጠለችበትን ታሪክ እንመረምራለን፡፡ ይህንን ትምህርት "**ውቅርና ይዘት**" የሚል ርእስ ሰጥተነዋል ምክንያቱም ሉቃስ ጽሑፉን እንዴት እንዳቀናጀ እና ሊያስተምረን የፈለገውን መልእክት እንመለከታለንና ነው፡፡

የሐዋርያት ሥራ ውቅርና ይዘት ምርመራችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ የመጽሐፉን የአጻጻፍ ስልት እንመለከታለን፣ በዚህም ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን የጻፈበትን ስልት መመልከታችን አተረጓጎማችንን እንዴት ሊቀርፀው እንደሚገባ እንመከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የመጽሐፉን ይዘት እናያለን፣ የጽሑፉን አደራደር በመመርመር እና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንዴት ሰዎች እንደሚረዱት እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ፣ የመጽሐፉን (ዘመነኛ ተዛምዶ) ናሙና እናቀርባለን፣ የሉቃስ ጥንታዊ መልእክት በእኛ ዘመን እንዴት በሥልጣን እንደሚናገር እንቃኛለን፡፡ አስቀድመን በሐዋርያት ሥራ የአጻጻፍ ስልት እንጀምር፡፡

# 2. የአጻጻፍ ስልት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለን መጽሐፍ ስናነብብ፣ ጸሐፊው የትኩረት ነጥቡን አንባቢዎቹ እንዲረዱለት የሚያግባባበትን መንገድ ማወቅ ይገባናል፡፡ ጸሐፊው ይህን መጽሐፍ ለምን ጻፈ? ጭብጡን ለመመሥረት የትኞቹን ባለሥልጣናት ይለማመናል? አንባቢዎቹ ወደ ትክክለኛው ድምዳሜ እንዲደርሱ ሊመራቸው መጽሐፉን የነደፈው እንዴት ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው ምላሽ ቸል ልንላቸው የማይገቡ በርካታ የአርቆ አስተዋይነት ጉዳዮችን አንግቧል፡፡

የሐዋርያትን ሥራ ስንቃረበው፣ በሉቃስ የአጻጻፍ ስልት ሦስት ገጽታዎች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ግልጽ ዓላማው እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ በሥልጣን ላይ ያለውን መተማመን እንጠቅሳለን፡፡ ሦስተኛ፣ በጠቅላላ መጽሐፉ ውስጥ ስላስቀመጣቸው ጥቂት መዋቅራዊ ንድፎችን እንነጋገራለን፡፡ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ለመጻፍ ያነሳሳውን ግልፅ ዓላማ በመመርመር እንጀምር፡፡

## ግልጽ ዓላማ

ሰዎች ረዘም ያለና በርካታ ነገሮችን ያዘለ ጽሁፍ ሲጽፉ፣ በርካታ ጉዳዮችንና ዓላማዎችን ያነግባሉ፡፡ ሉቃስም ባለ ሁለት ቅጽ ሥራዎቹን የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራን ሲጽፍ ነገሩ ለእርሱም እውነትነት አለው፡፡ የቴዎፍሎስንና የቤተክርስቲያንን ሕይወት በብዙ የተለያዩ መንገዶች ተፅዕኖ እንደሚያሳድርበት ተስፋ

ያደርግ ነበር፡፡ ስለዚህ ዓላማዎቹን ያለ ልክ እንዳናቃልላቸው መጠንቀቅ ይገባናል፡፡ ሉቃስ የሥራውን ዓላማ በግልፅ አስቀምቷል፡፡

ሉቃስ በሚጽፍበት ወቅት መንታ ዓላማዎች እንደነበሩት በግልፅ ማስቀመጡን እንመለከታለን፡፡ በአንድ ወገን፣ ታሪካዊ ዓላማ እንደነበረው ሉቃስ አውጇል፣ ያም በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ስለነበረችው ቤተክርስቲያን እውነተኛና አስተማማኝ ታሪክ የመጻፍ መሻት ነበረው፡፡ በሌላ ወገን፣ ወሳኝ ነገረ-መለኮታዊ ዓላማም እንደነበረውም አውጇል፤ ያም የወንጌልን መልእክት እውነታና ቁምነገር የማስተላለፍና የማረጋገጥ መሻት ነው፡፡ እውነተኛ ታሪካዊ ዘገባ የማቅረቡን መሻት በማስቀደም የሉቃስን ዓላማ መንታ ገፅታዎች እንመለከታለን፡፡

## ታሪካዊ መረጃ

በሉቃስ 1፡1-3 ለወንጌሉ በጻፈው መቅድም፣ ሉቃስ የመጀመሪያዊቱን ቤተክርስቲያን እውነተኛ ታሪክ የመጻፍ ቅን መሻት እንዳለው አመልክቷል፡፡ ንግግሮቹን አድምጡ፡

> ***የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ 1፡1-3)***

በዚህ ምንባብ ውስጥ ሉቃስ ለእውነተኛ ታሪክ ያለው ተቆርቋሪነት በበርካታ መንገዶች በግልፅ ታይቷል፡፡ በወቅቱ ስለተከናወኑት ታሪካዊ ክስተቶች ሲጽፍ “በኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር” በማለት ጠቅሶታል፡፡ ሉቃስ የዘገባውን ዝርዝሮች ሲያቀርብም “የዐይን ምስክሮችን” ያማከረ መሆኑንና “ሁሉን በጥንቃቄ” መመርመሩንም ጠቅሷል፡፡ የሚዘግበውም እውነት በግልፅና ያለስህተት ይተላለፍ ዘንድ “ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው” በማለት በጥንቃቄ ለመጻፍም ተጠንቅቋል፡፡

በአጭሩ፣ ሉቃስ በባለሁለት ቅፅ ሥራዎቹ በሉቃስ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራ ዒላማ ያደረገው እውነተኛ ታሪካዊ ዘገባን ማቅረብ ሲሆን፣ በወንጌሉ ስለ ኢየሱስ ሕይወት በመተረክ ይጀምርና በሐዋርያት ሥራ ደግሞ መቀጠሉን ይነግረናል፡፡ ሉቃስ እውነተኛ ታሪክ የመዘገብ ተቆርቋሪነት ነበረው፣ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግመው የተቀመጡ መርሆችን ማለትም፣ እግዚአብሔር ማንነቱን በእውነተኛ ታሪክ፣ ስፍራና ጊዜ ውስጥ ይገልጣል፣ የሚሉትን ስለተረዳ ነው፡፡ ማዳኑንና ፍርዱን ለማምጣት በታሪክ ውስጥ ይሠራል፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ በቅርብ ምዕተ-ዓመታት ውስጥ በርካታ ነቃፊ ምሁራን “ድነት”፣ “ፍርድ” እና “ታሪክ” የተሰኙት ጽንሰ-ሃሳቦች ጥቅል ናቸው ብለው ሙግት ያቀርባሉ፡፡ በጥቅሉ፣ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራዎች በታሪክ ውስጥ በተወሰነ ስፍራና ጊዜ አልተከናወኑም የሚል ድምዳሜን ያቀርባሉ፡፡ይልቁኑ ያ ታሪክ ተፈጥሮአዊ እንጂ መለኮታዊ አይደለም ብለው ያምናሉ፡፡ በውጤቱም፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱትን የእግዚአብሔር ሥራዎች ነቃፊ የነገረ-መለኮት ምሁራን ሲያነብቡ፣ እውነተኝነት የሌላቸው ሃይማኖታዊ በጎ ምኞቶች፣ “ሃይማኖታዊ ልብ ወለድ” አድርገው ይቆጥሯቸዋል፡፡

ሉቃስ ግን ሃይማኖታዊ ልብ ወለድ ለመጻፍ እንደማይጥር ይልቁኑ እውነተኛውን ታሪክ የመዘገብ ዓላማ እንዳለው በግልፅ አስቀምጧል፡፡ እንዲያውም፣ ያቀረበውን ማስረጃ ለማረጋገጥ ወይም ውድቅ ለማድረግ

በሚስችል መንገድ ጽፏል፡፡ አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ፣ ሉቃስ ትረካዎቹን እውቅ በሆኑ ታሪካዊ አውዶች መሃል አስፍሮታል፡፡በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ለምሳሌ በሐሥ 18፡12 ውስጥ ጋልዮስ፣ በ5፡34 ውስጥ ገማልያል፣ በ23፡26 ውስጥ ፊሊክስ በ24፡27 ውስጥ ደግሞ ፊስጦስ የተሰኙ ወንዶች የተጠቀሱ ሲሆን ሁሉም በጥንታዊው ይሁዶ ሮማዊው ዓለም የታወቁ ነበሩ፡፡ እነዚህንና ሌሎችን ታሪካዊ ዝርዝሮች በመጻፍ፣ አንባቢዎቹ በግላቸው ምርምሩን እንዲያረጋግጡት ሉቃስ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ አንባቢዎቹ ዘገባ ስላቀረበባቸው ሰዎችና ሁነቶች እውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር ሊነጋገሩ እና በተመሳሳይ ርዕስ ላይ የተጻፉ ሌሎች ጽሑፎችንም ሊያነብቡ ይችላሉ፡፡ የሉቃስ ዘገባዎች እውነተኛና ጭብጥ ባይሆኑ ኖሮ፣ ተጠራጣሪዎች በቀላሉ ያስተባብሏቸው ነበር፡፡

በተለይም ከ19ኛው ምዕተ-ዓመት ማብቂያ ጀምሮ፣ በርካታ ምሁራን የሐዋርያት ሥራን ታሪካዊ ትክክለኛነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ካሉ ምንባቦች እና ከሌሎች የከርሰ-ምድር ቅርስ ጥናቶች ጋር በማስተያየት መርምረውታል፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ብዙዎቹ ሉቃስ ተዓማኒ የታሪክ ፀሐፊ መሆኑን በበርካታ መንገዶች አመልክተዋል፣ ሁሉን ለመመልከት ጊዜ ስለሚገድበን ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ እንጠቅሳለን፡፡

በመጀመሪያ፣ በሐሥ 28፡7፣ ውስጥ ሉቃስ ግልፅ ታሪካዊ የቃል አገባብ እውቀቱን ገልጧል፡፡ በዚያ ስፍራ የሚሊጢን ደሴትን መሪ “የደሴት አለቃ” በማለት ይጠቅሰዋል፡፡ ይህ ያልተለመደ አባባል በየዘመናቱ ለበርካታ ተርጓሚዎች እንቆቅልሽ ሆኖባቸው ቆይቷል፣ የቅርብ ጊዜ የከርሰ ምድር ቅርስ ምርምር ግን ይህ ማዕረግ በወቅቱ ለመሪዎች ይሰጥ የነበረ እንደነበረ አሳይቷል፡፡

ሁለተኛ፣ በሐሥ 27፡21-26፣ ጳውሎስ በተሳፈረባት መርከብ ላይ ያከናወነው ተግባር የሰፈረው የሉቃስ ዘገባ በታሪካዊ ምርምር ተረጋግጧል፡፡ በዚያ ስፍራ ጳውሎስ ወደ ሮም ለመሄድ በተሳፈረባት መርከብ ውስጥ የተሳፈሩትን ሁሉ፣ በገጠማቸው ታላቅ ማእበል ወቅት እንደመከራቸውና እንዳበረታታቸው ሉቃስ ጽፏል፡፡ የቀደሙት ዘመናት ነቃፊ ምሁራን፣ እስረኛው ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ በግልጽ መናገር አይችልም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ ስለዚህም፣ ሉቃስ ሐዋርያውን የጀግን ማንነት ለማላበስ ይህን ልብ ወለድ ጽፏል ብለው ደመደሙ፡፡ በቅርብ ዓመታት የተደረጉ ምርምሮች ግን አንዲት መርከብ ከባድ አደጋ ውስጥ ስትወድቅ በመርከቡ የተሳፈረ የትኛውም ሰው የመርከቡን ሠራተኞች የመምከር ፈቃድ እንደሚሰጠው ያሳያል፡፡

እነዚህ ምሳሌዎች ሉቃስ ለታሪክ ጭብጦች የነበረውን ተዓማኒነት ይገልጣሉ፡፡ ጭብጥ ታሪካዊ እውነታዎችን የመዘገቡም ዓላማ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እውነት ከሕይወት ገሃድ እውነታዎች የተገነጠለ እንዳልሆነ ያሳስበናል፡፡ ይልቁኑ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት፣ ድነት የተገኘው በእውነተኛ ታሪክ ውስጥና አማካይነት መሆኑን ያሳየናል፡፡ ሉቃስ እውነተኛ ታሪካዊ ጭብጥ መጻፍን ዒላማ ያደረገው ለዚህ ነው፡፡

## የወንጌል መልእክት

የሉቃስን ታሪካዊ ዓላማ በልቡናችን ይዘን፣ የሉቃስን ዓላማ ሁለተኛ ገፅታ ማለትም በሐዋርያት ሥራ የተላለፈውን የወንጌል መልእክት እውነታና ኃይል የማስተላለፉን ነገረ-መለኮታዊ ዓላማ እንመረምራለን፡፡ በሉቃስ 1፡3-4 የተጻፈውን አንድ ጊዜ አድምጡ፡

> ***በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ። (ሉቃስ 1፡3-4)***

በዚህ ስፍራ እንደምናየው፣ ሉቃስ የሐዋርያትን ሥራ ታሪክ የጻፈው ሌዎፍሎስና ሌሎች ስለተማሩት ነገር እርግጡን እንዲያውቁ ነው፡፡ ይህም ማለት የሐዋርያት ሥራ የሃይማኖት ማስተማሪያ መጽሐፍ ወይም

ትምህርት አዘል ጽሑፍ ነው ማለት ነው፡፡ ቴዎፍሎስም ሆነ ሌሎቹ አንባቢዎቹ አንዳንድ ጭብጦችን፣ ነገረ-መለኮታዊ ቁርጠኝነቶችን በሐዋርያት ሥራ ስለጻፋቸው ታሪካዊ ድርጊቶች ነገረ-መለኮታዊ ፋይዳ እንዲያውቁ ሉቃስ ይፈልጋል፡፡

ቀደም ባለው ትምህርት እንዳየነው፣ ሉቃስ ዓለምንና ታሪክን በጠቅላላ የሚመለከተው በክርስቶስ ጌትነትና መንግሥት መነፅር ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ተስፋዎችና ቃል ኪዳኖች በኢየሱስና በቤተክርስቲያን አማካይነት እንደተፈፀሙ አይቷል፡፡ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የተከናወኑ ድርጊቶችን የዘገበበትን ዘገባ ቴዎፍሎስ በዚህ መነፅር አማካይነት እንዲመለከት፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት፣ እንዴት መንግሥቱን እንደመሠረተና የእግዚአብሔር መንግሥት ግንባታ ሥራውን በክርስቶስ መቀጠሉን እንዲያስተውል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ፣ ዛሬ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ስናነብብ፣ ሉቃስ እንዲያው ዝም ብሎ እውነተኛ ጭብጦችን በመዘገብ ከብዙ ዓመታት በፊት ምን እንደተከናወነ እንድናውቅ ብቻ እንዳልጻፈ ልብ ልንል ይገባናል፡፡ ይልቁኑ ለቤተክርስቲያን መሠረታዊ የሆኑ አስተማሪዎችን እንድናስተውላቸው ዒላማ አድርጎ ጽፏል፡፡ ይህም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለ ቀጠለው የክርስቶስ ሥራ አስተማማኝ ምስክርነት መስጠት መው፡፡

# በሥልጣን መደገፍ

የሉቃስን መንታ ዓላማ በልቡናችን ይዘን፣ የአጻጻፍ ስልቱን ሁለተኛ ገጽታ፣ ማለትም በሥልጣን ላይ ያለውን መተማመን ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡ ሉቃስ የሚዘግባቸውን ታሪካዊና ነገረ-መለኮታዊ እውነቶች የሚያረጋግጠው በራሱ ሥልጣን ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን፣ በክርስቶስና በሐዋርያት ሥልጣን ላይ ነው፡፡ በዚህ መንገድ፣ ሉቃስ የወንጌል እውነተኛ ምስክር ሆኗል፡፡

በሐዋርያት ሥራ አስገራሚ የሆነው አንድ ነገር የክርስቶስ ቁልፍ ምስክሮች ሆነው ያገለገሉ ሰዎች ለተናገሯቸውና ላከናወኗቸው ነገሮች የተሰጠው ሰፊ ሽፋን ነው፡፡ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሲርግ፣ ሐዋርያቱ የእርሱ ምስክሮች እንዲሆኑ ጠራቸው ሥልጣንም ሰጣቸው ደግሞም በእርሱ በመታመን የመንግሥቱን ሥራ እንዲቀጥሉ አዘዛቸው፡፡ ነቢያትና አዕማድ የሆኑት የቤተክርስቲያን መሪዎች የእርሱን መልእክት ያውጁ ዘንድ በየጊዜው ኃይልን ያለብሳቸው ነበር፡፡ ሉቃስ ቴዎፍሎስንና ሰፊዩቱን ቤተክርስቲያን ስለ አመለካከቱ ሲያግባባቸው አመለካከቶቹን ለመግለፅና በሥልጣን የተደገፉ ለማድረግ መልሶ መላልሶ የቀደመችውን ቤተክርስቲያን መሪዎች፣ በተለይም ሐዋርያትንና ነቢያትን ይጠቅሳል፡፡

ሉቃስ በሥልጣን ላይ የነበረውን መደገፍ በዝርዝር ለመመርመር፣ በሁለት ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሉቃስ ከባለሥልጣን ቃላት ጋር ያለውን ቁርኝት እናያለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በሥልጣን የተከናወኑ ተግባራትን ያጣቀሰበትን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ ሉቃስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን ላነገቡ ቃላት የሰጠውን አፅንዖት በመመልከት እንጀምር፡፡

## ቃላት

ቀደም ባለው ትምህርታችን እንደጠቀስነው፣ ሉቃስ ሐዋርያ አልነበረም፡፡ ወደ እምነት የመጣው ምናልባት ጌታ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከጳውሎስ ጋርና ጳውሎስ በሌለበትም ባደረጋቸው ጉዞዎች፣ የኢሱስንና የሐዋርያቱን አገልግሎት መርምሯል፣ የጌታ ምርጥ የዐይን ምስክሮችን ምስክርነትም ዘግቧል፡፡

በአንድ በኩል፣ ሁሉም የክርስቶስ ተከታዮች ምስክሮቹ ናቸው፡፡ ቤተክርስቲያን ስትመሠረት ግን፣ ሐዋርያቱ የማይሻሩ ምስክሮቹ እንዲሆኑ ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሾሟቸዋል፡፡ እርሱ በሌበት ዘመን በምድር ላይ ቋሚና

ባለሥልጣን ምስክሮቹ እንዲሆኑ የሾማቸውና ኃይልን የሰጣቸው እነርሱ ብቻ ነበሩ፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን፣ ነቢያትንና ሌሎችን ሥልጣን ያላቸውን፣ እንደ ሉቃስ ያሉ፣ የቤተክርስቲያን መሪዎችን፣ በአንዳንድ ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ በሥልጣን እንዲመሰክሩ ጌታ ጠርቷቸዋል፡፡

ሉቃስ ሥልጣን የተላበሱ ቃላትን ያቀረበበት ዋነኛ መንገድ ንግግሮችን በቀጥታ መዘገብ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን አስተምህሮዎች ላይ ሃሳብ ከመሰንዘር ይልቅ፣ ሉቃስ ዘወትር ዝርዝርን ንግግሮችን በመዘገብ፣ የጌታ ባለሥልጣን ወኪሎች በታሪኩ ውስጥ ንቁ ገፀ-ባሕርያት ሆነው ስለ ራሳቸው እንዲናገሩ ፈቅዶላቸዋል፡፡

እንዲያወም፣ የሐዋርያት ሥራ 30% ያህሉ ክርክሮች፣ ሙግቶች፣ ጭውውቶች እና መነባንቦች፣ ስብከቶች እና ሌሎች የቃል ንግግሮች ናቸው፡፡ በሌሎች ጥንታዊ ትረካዎች ከምናገኛቸው ይልቅ በብዙ መቶኛ በንግግር የተሞላ ጽሑፍ ሲሆን ይህም የሆነው የሐዋርያትን ስለጣን ለማስረገጥ ሉቃስ በንግግር ላይ ታምኗል፡፡ በድምሩ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ 24 ንግግሮች አሉ፡ ስምንቱ ከጴጥሮስ፣ ዘጠኙ ከጳውሎስ፣ አንዱ ከእስጢፋኖስ፣ አንዱ ከያዕቆብ እና ጥቂት ከሌሎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ንግግሮች አብዛኛው የሐዋርያት ንግግሮች ናቸው፣ የተቀሩት ግን በነቢያትና እውቅ በሆኑ መሪዎች የተነገሩ ናቸው፡፡

ይህ ግን ለምን ወሳኝ ሆነ? በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙ ንግግሮች የቀደመችው ቤተክርስቲያን መሪዎች እነማን እንደነበሩ እና ስለ በርካታ ጉዳዮች ምን እንዳስተማሩ ይነግሩናል፡፡ ደቀመዛሙርት ስለ ክርስቶስ ለመሰቃየት ለምን ፈቃደኛ እንደሆኑ ያሳዩናል፡፡ ሐዋርያት ለክርስቶስ ስለሰጡት አገልግሎት ይመሰክሩልናል ደግሞም መንግሥቱን ለመመሥረት የሚያስችል መመሪያም አንግበዋል፡፡ በተጨማሪም ሉቃስ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ታሪክ ላይ ያለውን አመለካከት አረጋግጠውለታል፡፡

በ19ኛውና በ20ኛው ክፍለ ዘመን የሚገኙ በርካታ ነቃፊ ሊቃውንት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስላካተታቸው ንግግሮች እውነተኛ ዘገባ አቅርቧል የሚለውን አይቀበሉም፡፡ በጥንታዊው ዓለም ታሪካዊ ዘገባዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ንግግሮች ቃል በቃል የተቀዱ ዓይነት ጭብጦች እንደማይሆኑ በርካታ ምሳሌዎችን እናገኛለን፡፡

ሆኖም ከሉቃስ በፊት፣ በእርሱ ዘመንና በኋላ የነበሩ ነቃፊና ወንጌላውያን ምሁራን በታሪካቸው ውስጥ የሚያካትቷቸው ንግግሮች እውነተኞቹን ንግግሮች በትክክል የሚወክሉ እንዲሆኑ ለማድረግ በብርቱ ይሠሩ እንደ ነበር ያመለክቱናል፡፡ እንዲያውም፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተመዘገቡትን ንግግሮች በቅርበት ስናጠናቸው፣ ሉቃስ ከእነዚያ ተዓማኒ የታሪክ ጸሐፍት አንዱ እንደነበር አሳማኝ መረጃ እናገኛለን፣ ስለዚህ እርሱ ያካተታቸው ዘገባዎች ሥልጣን ያላቸውን ሐዋርያዊ አስተምህሮዎች የሚወክሉ ናቸው፡፡

በቅድሚያ በሐዋርያት ሥራ በተመዘገቡት ንግግሮች የምንተማመንበት ምክንያት የማይሻርና ሥልጣን የተላበሰ ታሪክ እንዲመዘግብ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ የተነዳ በመሆኑ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ፣ በሐዋርያት ሥራ የተመዘገቡት ንግግሮች የቀጥተኛ ንግግሮቹ እውነተኛ ወኪሎች መሆናቸውን የምናረጋግጥባቸው ቢያንስ አራት ሌሎች መንገዶች አሉን፡፡

አንደኛ፣ ንግግሮቹ የራሳቸው ዘይቤ አላቸው፡፡ በሐዋርያት ሥራ ካሉት ከሌሎቹ ዘገባዎች ጋር ስናስተያያቸው፣ ተፈጥሮአዊና ቀለላ ያለ ዘይቤ ያላቸው ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ ግርድፍና ያልተቀባቡ ግሪከኞች ናቸው፡፡ ይህም ሉቃስ ትኩረት ያደረገው ተናጋሪዎቹ በእርግጥ ሊናገሩ የፈለጉትን በመዘገቡ ላይ ስለነበር ንግግሮቻቸውን ለማሻሻልና ለመቀባባት አልሞከረም፡፡

ሁለተኛ፣ ንግግሮቹ ከሚወክሏቸው አውዶች ጋር የሚጣጣሙ ነበሩ። እያንዳንዱ ንግግር ከተናጋሪውና ከአድማጩ ጋር መርፌና ክር ነበሩ። ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ 4 ውስጥ፣ ጴጥሮስ ሽባውን ከፈወሰ በኋላ ከአይሁድ መሪዎች ጋር ተነጋግሯል። ምንም አንኳን ንግግሩ ድነት በክርስቶስ መሆኑን ቢያውጅም፣ ፈውሱ የሚናገረው ማረጋገጫ እንደሆነ ጴጥሮስ በቀጥታ ተናግሯል። ከዚያም ባሻገር፣ የማያምኑት የአይሁድ መሪዎች ጴጥሮስን ሊያስተባብሉበት አልቻሉም ምክንያቱም እነርሱ ራሳቸው የፈውሱ ምስክሮች ነበሩ። ስለዚህ እኛ ልናስብ እንደምንሞክረው የሉቃስ ፈጠራ አልነበረም። በተመሳሳይ መንገድ፣ የጳውሎስ ንግግሮች የአድማጮቹን አውድ የጠበቁ ነበሩ። ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ 13 በጵስድያዋ አንጾኪያ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚፈሩት ጋር የተነጋገረው ከኢስጢኢኮች እና ከኤፊቆሮስ ፈላስፎች ጋር በሐሥ 17 ካደረገው በተለየ መንገድ ነበር።

ሦስተኛ፣ እያንዳንዱ ንግግር የተናጋሪውን የግል ነገር የሚያንፀባርቅ ነው። የጋራ የሆኑ መሪ ሃሳቦችን ቢያነግቡም፣ እያንዳንዱ ተናጋሪ የየራሱ የተለየ መለያ ነበረው። ለምሳሌ፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን መሪዎች በሐሥ 20 ያደረገው ንግግር ከጳውሎስ ደብዳቤዎች ጋር የሚያስገርሙ ጉድኝቶችን ይዟል። እነዚህን ደብዳቤዎች ከጻፈ ሰው የሚጠበቅ ዓይነት ንግግር ነው።

አራተኛ፣ በአንዳንድ ስፍራዎች፣ አንዳንድ ንግግሮችን ጠቅለል እና አጠር እንዳደረጋቸው በግልጽ ሉቃስ በግልፅ አመልክቷል። ለምሳሌ፣ በሐሥ 2፡40፣ ጴጥሮስ ሌሎች "**ብዙ ቃሎችን**" እንደተናገረ ጠቅሷል። ተደራሲያኑ አንዳንድ ጊዜ የአንዳንድ ንግግሮችን ሙሉ ይዘት ሊያገኙ እንደማይችሉ ሉቃስ በዓላማ እያነቃ ያመለክታቸዋል። ይህም ሉቃስ ዒላማ አድርጎ የነበረው የንግግሮቹን ሙሉ ሃሳብ ያነገቡ ወካይ ሃሳቦችን እንደየአውዳቸው ማቅረብ ነበር ወደሚለው እንድናደላ ያደርገናል።

በእነዚህና በሌሎችም በርካታ መንገዶች፣ ሉቃስ ትክክለኛ ታሪካዊ እውነትነት ያላቸው ንግገሮችን አቅርቦልናል በሚለው እንተማመናለን። ዓላማውን ለማሳካት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የራሱን የፈጠራ ሥራ አልደነጎረም ወይም አልፈበረከም ማለት ነው። ይልቁኑ፣ የእርሱን ሃሳቦችና የትረካ መግለጫዎች ያሳረፈው ሥልጣን ባላቸው ሐዋርያት ምስክርነት ላይ ነበር።

ባለሥልጣን ቃላትን ከማስፈሩ በተጨማሪ፣ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ በጠቅላላ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ነገረ-መለኮታዊ መልእክት ለመደገፍ በቀደመችው ቤተክርስቲያን የተከናወኑ ድርጊቶችንም ዘግቧል።

## *ሥራዎች/ ድርጊቶች*

መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያትን በኃይል ስላስታጠቃቸው፣ በቀደመችው ቤተክርስቲያን የነበሩ አዕማድ መሪዎችና ነቢያት የሚያስተላልፉትን የወንጌል መልእክት በበርካታ መንገዶች በተዓምራት ያረጋግጡ ነበር። በመንፈሳዊ ስጦታዎች በተሞሉ ፈውሶች፣ ሙታንንም በማስነሳት የተዓምራት ሥራዎች፣ ሐዋርያት የክርስቶስ ባለሥልጣን አምባሳደሮች እንደነበሩ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክር ነበር።

በሐሥ 13፡7-12፣ በጳፉ አገረ ገዥ ፊት የጳውሎስ አገልግሎት የተረጋገጠበትን ታሪክ እንመልከት። በዚያ ስፍራ ሉቃስ ያሰፈረውን አድምጡ፡

> ***እርሱም አስተዋይ ሰው ከሆነው ሰርግዮስ ጳውሎስ ከሚባለው አገረ ገዥ ጋር ነበረ። ይህም በርናባስንና ሳውልን ወደ እርሱ ጠርቶ የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰማ ፈለገ።***
> ***ጠንቋዩ ግን ኤልማስ፥ ስሙ እንዲሁ ይተረጐማልና፥ አገረ ገዡን ከማመን ሊያጣምም ፈልጎ ተቃወማቸው።***
> ***ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኵር ብሎ ሲመለከተው።***

*አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፥ የዲያብሎስ ልጅ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፥ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን?*
*አሁንም፥ እነሆ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፥ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት፥ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ።*
*በዚያን ጊዜ አገረ ገዡ የተደረገውን ባየ ጊዜ ከጌታ ትምህርት የተነሣ ተገርሞ አመነ። (ሐሥ 13፡7-12)*

ኤልማስ የወንጌል እንቅፋት ሊሆን ሲሞክር፣ በዐይነ-ስውርነት እንዲመታ ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን ኃይል ሞላበት፡፡ እናም የጳውሎስ ትምህርትና ተግባር አገረ-ገዢው የወንጌሉ መልእክት እውነት እንደሆነ እንዲቀበል አስችሎታል፡፡

ሉቃስ ባለሥልጣን ቃሎችንና ተግባሮችን የዘገበው አንባቢዎቹን ስለ ጽሑፉ እውነተነት ለማግባባት ነው፡፡ ሐዋርያት ክርስቶስ ሥልጣን የሰጣቸው መሆኑን እና በሁሉም ስፍራና ትውልድ መካከል የምትገኘውም ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት በክርስቶስ በመታመን ስታስፋፋ የእነርሱን ምስክርነት የመከተል ግዴታ እንዳለባት አንባቢዎቹ እንዲያስተውሉ ይፈልጋል፡፡

የሉቃስን ግልፅ ዓላማና በሥልጣን ላይ የነበረውን መደገፍ ከተመለከትን፣ ወደ ሉቃስ የአጻጻፍ ስልት ሦስተኛ ክፍል እንሸጋገር፡፡ ይህም በጠቅላላው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሉቃስ የተከተለው የአወቃቀር ንድፍ ነው፡፡

# የአወቃቀር ንድፍ

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በርካታ የአወቃቀር ንድፎች አሉት፣ ከጊዜ የተነሣ ግን በሁለቱ የሐዋርያት ሥራ ገፅታዎች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ወሳኝ የሆኑ ተደጋጋሚ የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገሮችን እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኘውን የቤተክርስቲያን እድገት ንድፍ እንመለከታለን፡፡ ሉቃስ የተጠቀመባቸውን የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገሮች በመመልከት እንጀምር፡፡

## ጥቅል ዐረፍተ-ነገሮች

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት በትረካዎች ውስጥ እነርሱም ያሉበት መሆኑን በተለያዩ እርከኖች ያሳውቃሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ፣ ለሁሉም ተግባራዊ ዓላማዎች፣ ራሳቸውን ከታሪኩ ትዕይንት በስተጀርባ ይደብቃሉ፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ በዘገባቸው ውስጥ እየተከናወነ ስላለው ነገር ግልፅ ሃሳብ ለማቅረብ በይፋ ራሳቸውን ይገልጣሉ፡፡ ይህንንም የጸሐፊው ሃሳብ የሚቀርብበት ዘዴ ብለን እንጠራዋለን፡፡ ሉቃስም በጠቅላላው የሐዋርያት ሥራ ውስጥ በርካታ የጸሐፊ ሃሳቦችን አስፍሯል፡፡ ስለ ዳራው መረጃ ያቀርብልናል፣ የገፀ-ባህርያቱን ልብ ገልጦ ያሳየናል፣ መቼቶችንና ሌሎችንም ጉዳዮች ያብራራልናል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው መልእክቱ በግልፅና በታማኝነት እንዲቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ በዘገባቸው ድርጊቶች ላይ ሃሳቡን የሚሰነዝረው በማጠቃለያ አረፍተ ነገሮች አማካይነት ነው፡፡

ስለ ማጠቃለያ አረፍተ ነገሮች ወደኋላ ላይ የበለጠ እንመለከታለን፣ ለአሁኑ ግን፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በምናገኛቸው በርካታ የመሸጋገሪያ ነጥቦች፣ የወንጌልን መስፋፋትና የቤተክርስቲያንን ሁኔታ ሉቃስ እንዴት

ጠቅለል አድርጎ እንዳቀረበ እንመለከታለን፡፡ እያንዳንዱ ማጠቃለያ በወቅቱ ለተጠቀሰበት ጉዳይ የራሱ ሆነ መለያ ቢኖረውም፣ በአንድነት ተያይዞ መላልሶ የሚገለጥ መሪ ሃሳብ ያነግባል፡፡

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ተነስቶ እንዴት እንደተስፋፋ የሚገልጥ መሆኑን በርካታ ተደራሲያን ያስተውላሉ፡፡ ሉቃስም ወደዚህ ዋና ነጥብ ለመድረስ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ ቆም ይልና ድርጊቶቹን ጠቅለል አድርጎ ያቀርባቸዋል፡፡ ሉቃስ በታሪኩ ውስጥ ስድስት ያህል ወሰነ-ጊዜያትን ማጠቃለያ እንዴት እንደሠራላቸው እንመረምራለን፡፡ እነርሱም፡ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ የወንጌል መስፋፋት፤ ከሰማርያ እስከ ሶርያዋ አንፆኪያ፣ በቆጵሮስ፣ በፍርግያ እና በገላትያ፤ በእስያ በመቄዶኒያ እና በአካይያ እና ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም እንዴት እንደተስፋፋ የሚተርኩት ናቸው፡፡

በኢየሩሳሌም በምትገኘው ቤተክርስቲያን ስለታየው እድገት ሉቃስ ስድስት ወሳኝ የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገሮችን ያቀርብልናል፡

1. በሐሥ 2፡42-47 ከጴጥሮስ የበዓለ ሃምሳ ስብከትና ከሦስት ሺህ አማኞች መጠመቅ በኋላ
2. በ4፡32-37 አማኞች በመከራ መሃል ድፍረትን እንዲሰጣቸው ከፀለዩ በኋላ
3. በ5፡11-16 በሃናንያና በሰጲራ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ካረፈባቸው በኋላ
4. በ5፡42 ሐዋርያት በሸንጎው ፊት በድፍረት ከቆሙ በኋላ
5. በ6፡7 የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት ከተመረጡ በኋላ
6. በ8፡4 ከእስጢፋኖስ መሰዋትና ከጳውሎስ መሰደድ በኋላ

የእነዚህን የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገሮች ተፈጥሮና ተግባር ለማብራራት፣ በኢየሩሳሌም ከተከናወኑ ድርጊቶች ማጠቃለያዎች መካከል አንዱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 5፡42 ሉቃስ ስለ ቤተክርስቲያን መስፋትና እንቅስቃሴ ያቀረበውን ማጠቃለያ እንውሰድ፡

> ***ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር። (የሐሥ 5፡42)***

ሉቃስ በጠቅላላው የሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚሰጣቸውን እነዚህን የመሰሉ ማጠቃለያዎችን አዘውትሮ የሚያቀርበው የወንጌልን የግስጋሴ ደረጃዎች እና የቤተክርስቲያንን እድገት ሊያሰምርበት ነው፡፡ ሉቃስ በይሁዳና በሰማርያ የተከናወኑ ድርጊቶችን የዘገበው በተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡

1. በሐሥ 8፡25 ሐዋርያት በሰማርያ ካገለገሉ በኋላ፣
2. በሐሥ 8፡40 ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከተጠመቀ በኋላ፣
3. በሐሥ 9፡31 ከሳውል መለወጥ በኋላ

በሐሥ 12፡24 ወንጌል በፊንቄ፣ በቆጵሮስና በአንጾኪያ ስለ መስፋፋቱ ሉቃስ ማጠቃለያ ሰጥቷል፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ ወንጌል በቆጵሮስ፣ በፍርግያ እና በገላትያም ስለ መስፋፋቱ በሐሥ 15፡35 ሉቃስ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ በእስያ፣ በመቄዶንያና በአካይያ ወንጌል የመስፋፋቱን ታሪክም በማጠቃለያው ደምድሞታል፡፡

1. በሐሥ 16፡5 ጳውሎስና ሲላስ ከሰበኩና ለተለወጡ ወጣቶች መመሪያ ከሰጡ በኋላ

2. በሐሥ 19፡20 ጳውሎስ በኤፌሶን ካገለገለ በኋላ

ሉቃስ የመጽሐፉን የመጨረሻ ክፍል የደመደመው፣ ወንጌል ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም እንዴት እንደዘለቀ፣ በተናገረበት ከሁሉ እጅግ በሚልቀው የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገር ነው፡፡ በሐስ 28፡30-31 የተናገረውን አድምጡ፡

> ***ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፤***
> ***ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር። (የሐሥ 28፡30-31)***

ሉቃስ በሚሰጣቸው የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገሮች የሠዎችን ትኩረት ወደሚናገረው የታሪክ ገፅታ የሚስብ መሆኑን ከተመለከትን፣ በእነዚህ የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገሮች መካከል የተገለጡትን የቤተክርስቲያን እድገት ንድፎች መመልከት ይገባናል፡፡

## የቤተክርስቲያን እድገት

ሉቃስ የቤተክርስቲያንን እድገት ሲዘግብ፣ ሁለት መንታ ብርቱ ኃይላትን አዘውትሮ ይጠቅሳል፡፡ በአንድ በኩል፣ ስለ ቤተክርስቲያን ውስጣዊ እድገትና ውጥረት ይጽፋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለ ውጫዊ እድገትና ከውጭ ስለ ገጠማት ተቃውሞ ጽፏል፡፡ የዚህን ንድፍ በዚህ ትምህርት ውስጥ ወደ ኋላ ላይ የምንጠቅስ ሲሆን፣ ለአሁኑ ግን ምን ማለታችን እንደሆነ በቀላሉ እንገልጻለን፡፡

**"ውስጣዊ እድገት"** ስንል፣ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ውስጥ ወንጌል ስላመጣው በጎ ተፅዕኖ መግለጣችን ነው፡፡ ይህንም ስንል የቁጥር እድገትን፣ የግለሰቦችን አልፎም የቤተክርስቲያንን በጥቅሉ መንፈሳዊ ብስለት ማለታችን ነው፡፡ "ውጥረት" ስንል ደግሞ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱትን ችግሮች፣ ጥያቄዎች፣ አምባጓሮዎች እና ትግሎች በልቡናችን ይዘን ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ በውስጣዊ እድገትና ውጥረት መካከል ተለዋዋጭ ግንኙነት መኖሩን ሉቃስ አዘውትሮ ይጠቅሳል፡፡ ውስጣዊ እድገት ወደ ውጥረት ያመራል፣ ውጥረት ደግሞ ወደ እድገት ያመራል፡፡

በሉቃስ መዋቅራዊ ቅርፅ ውስጥ የምናየው ሁለተኛው ጥንድ ውጫዊ እድገትና ተቃውሞ ነው፡፡ "ውጫዊ እድገት ስንል"፣ ቤተክርስቲያን በቁጥር የምትበዛው አዳዲስ አማኞችን ስትጨምር ነው ማለታችን ነው፡፡ ይህ መሰሉ እድገት የቁጥር እድገት ነው፡፡ "ተቃውሞ" ስንል የማያምኑ ሰዎች ለወንጌል አሉታዊ ምላሽ በሚሰጡበት ወቅት በቤተክርስቲያንና በማያምነው ዓለም የሚነሳውን የግጭት እውነታ ማመልከታችን ነው፡፡ በዚህኛው እንደገና፣ በሐዋርያት ሥራ በእነዚህ ሁለት ሃሳቦች መካከል ተለዋዋጭ ግንኙነት አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ውጫዊ እድገት ወደ ተቃውሞ ሲያመራ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ተቃውሞ ወደ ውጫዊ እድገት ያመራል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ በእነዚህ መንታ ጥንዶች መካከል፣ ማለትም በአንድ ወገን በውስጣዊ እድገትና ውጥረት መሃል፣ በሌላ ወገን ደግሞ ውጫዊ እድገትና ተቃውሞ መካከል ተለዋዋጭ ግንኙነት እንዳለ ሉቃስ ደጋግሞ ያመለክታል፡፡ በሌላ አባባል፣ ውስጣዊ እድገትና ውጥረት ወጫዊ እድገትንና ተቃውሞን ሲያስከትል፣ ውጫዊ እድገትና ተቃውሞ ደግሞ፣ውስጣዊ እድገትና ውጥረት እንደሚያስከትል ሉቃስ ዘወትር ያመለክታል፡፡ በዚህ ትምህርት ወደኋላ ላይ እንደምንመለከተው፣ ይህ የቤተክርስቲያን እድገት ንድፍ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተደጋጋሚ ይታያል፡፡ ያም የመጽሐፉን ፅንሰ-ሃሳባዊ አመለካከት ወይም መዋቅር ይቀርፀዋል ማለት ነው፡፡

በመጽሐፉ በጠቅላላ ሉቃስ የሚያቀርባቸው ማጠቃለያዎች የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ዐቢይ ክፍሎች ማለትም በመጀሪያዪቱ ቤተክርስቲያን አማካይነት ወንጌል እንዴት እንደተስፋፋ የሚያነሳቸውን ሃሳቦች በግልጽ ያመለክታሉ፡፡ እነዚህ ሃሳቦች በቴዎፍሎስና በሌሎችም መጽሐፉን በሚነብቡ ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ መገመት ትችላላችሁ፡፡ ውጥረቱ ወይንም ተቃውሞው የቱንም ያህል ቢበረታ፣ እግዚአብሔር የቤተክርስቲያንን ውስጣዊ እና ውጫዊ እድገት በወንጌል አማካይነት ለማምጣት ዘወትር በሥራ ላይ እንዳለ በማሳየት በየትኛውም ስፍራ የሚገኙትን አማኞች ያበረታታሉ፡፡ የቀደሙት ክርስቲያኖች ታሪክን በዚህ ዓይነት አመለካከት እንዲያነብቡ ወደማሳሰቡ ያዘነብላሉ፡፡ ከውስጥና ከውጭ ችግሮቻቸው ባሻገር ለጌታቸውና ለአዳኛቸው ታማኝ ምስክሮች ሆነው ከዘለቁ፣ በእነርሱም ዘመን የወንጌልን እድገት እንደሚመለከቱ ያረጋግፁላቸዋል፡፡

# 3. ይዘት

የሉቃስን አጻጻፍ ስልት ጥቂት ማዕከላዊ ሃሳቦችን በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ሁለተኛው ርዕሳችን ማለትም ወደ ሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይዘት ዘወር እንላለን፡፡ የዚህን መጽሐፍ ይዘት ጠቅለል የምናደርግባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ የቤተክርስቲያን እድገት የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር የመምጣቷ ከፊል እውነታ መሆኑን ሉቃስ ባቀረበበት መንገድ ላይ እናተኩራለን፡፡

የሉቃስ ባለሁለት ቅጽ ሥራዎች የሆኑት የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ ወንጌልን በማወጅ ኢየሱስ እንዴት የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደጀመረና በምድር እንደገነባ ያብራራሉ፡፡ በወንጌሉ፣ በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት ኢየሱስ የመንግሥቱን ወንጌል መሠረት እንዴት እንደጣለ ሉቃስ አብራርቷል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ደግሞ፣ የእርሱን የመንግሥት ግንባታ ሥራ ሐዋርያትና ቤተክርስቲያን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ኢየሱስ እንዴት መንፈስ ቅዱስን እንዳፈሰሰ ሉቃስ ገልጾአል፡፡ በዚህ መንገድ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የሉቃስ ባለሁለት ቅፅ ሥራዎች ማእከላዊ ታሪክ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፣ የሐዋርያት ሥራን ይዘት ስንመረምር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሐዋርያት አመራር መስፋፋቱን የቀጠለበትን መንገድ እናተኩርበታለን፡፡

ኢየሱስ በሐሥ 1፡8 ሐዋርያቱን ሲልካቸው፣ ከኢየሩሳሌም ጀምረው፣ በመላው ዓለም ወንጌልን በመስበክ ምስክሮቹ በመሆን እንዲያገለግሉ አዟቸዋል፡፡ ኢየሱስ በሐሥ 1፡8 ለሐዋርያቱ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (የሐሥ 1፡8)***

በዚህ ስፍራ ቤተክርስቲያን የወንጌል ምስክር የምትሆንበትን መልክዓ-ምድራዊ ስልት ኢየሱስ አስቀምጧል፡፡ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመመላት፣ ምስክርነታቸውን በኢየሩሳሌም ጀምረው፣ ከዚም ወንጌሉን ወደ ሰማርያና ወደ ይሁዳ ሊያደርሱ በመጨረሻም እስከ ምድር ዳር ድረስ፣ በየደረሱበት ሁሉ መንግሥቱን ሊያሰፉ ይገባ ነበር፡፡

በርካታ ምሁራን እንደሚገልፁት ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን ያቀናጀው ኢየሱስ ለመልክዓ-ምድራዊ የምስክርነት መስፋፋት ባቀረበው ጥሪ ዙሪያ መሆኑን ደርሰውበታል፡፡ እኛም ሥራውን ስንዳስስ፣ ተመሳሳዩን ንድፍ ልንከተል ይገባናል፡፡ በመጀመሪያ ወንጌል በኢየሩሳሌም የተስፋፋበትን መንገድ በሐዋርያት ሥ1፡1-8፤4 ውስጥ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ መንግሥቱ በይሁዳና በሰማርያ መንግሥቱ እያደገ መሄዱን በሐሥ 8፡5-9፡31 ውስጥ እንመለከታለን፣ ሦስተኛ ደግሞ፣ በሐሥ 9፡32-28፡31 ቤተክርስቲያን

ወንጌሉን ወደ ምድር ዳርቻ በወሰደችበት መንገድ ላይ እናተኩራለን፡፡ ይህ ሦስተኛው ክፍል ረጅም በመሆኑ ምክንያት፣ ልዩ አትኩሮት በማድረግ፣ ሉቃስ የማጠቃለያ ዐረፍተ-ነገር በሰጠባቸው አራት የእድገት እርከኖች ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣በፊንቄ፣ በቆጵሮስ እና በአንፆኪያ የተከናወነውን በሐሥ 9፡32-12፡25፤ ሁለተኛ፣ በቆጵሮስ፣ በጲርግያ እና በገላትያ የተከናወነውን በሐሥ 13፡1-15፡35፤ ሦስተኛ፣ በእስያ፣ በመቄዶኒያ እና በአካይያ ውስጥ የተከናወነውን በሐሥ 15፡36-21፡16፤ አራተኛ ደግሞ፣ ወደ ሮም በተደረገው ጉዞ የተከናወነውን በሐሥ 21፡17 እስከ 28 ቁጥር 31 ውስጥ እናገኛለን፡፡

በውስጣዊ እድገትና ውጥረት ደግሞም በውጫዊ እድገትና ተቃውሞ ላይ በማተኮር እነዚህን ዝርዝሮች በበለጠ ጥልቀት እንመለከታለን፡፡ በሐሥ 1፡1-8፡4 በሐዋርያቱ የወንጌል ምስክርነት አማካይነት መንግሥቱ በኢየሩሳሌም የተመሠረተበትን መንገድ በመመልከት እንጀምር፡፡

# ኢየሩሳሌም

ኢየሩሳሌም በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ልዩ ህዝብ፣ የጥንታዊቷ እስራኤል ዋና ከተማ ነበረች፡፡ ኢየሩሳሌም ለሉቃስ ዘገባ መነሻ የነበረች ስፍራ ናት ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን በነበረው የእግዚአብሔር መንግሥት እና በኢየሱስ አገልግሎት ማእከላዊ ስፍራ የነበራት ስፍራ ነበረች፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሌሎች ስፍራዎች ውስጥ ሉቃስ በኢየሩሳሌም ስለተከናወኑ ድርጊቶች የጻፈ ሲሆን፣ ወንጌልን ወደ ሌሎች ምድሮች የመውሰዱ የሐዋርያት ሥራ ስር የሰደደው በዚህችው ልዩ ከተማ እንደነበር ዘአውትሮ ያሳየናል፡፡

በወንጌል አገልግሎት መንግሥቱ በኢየሩሳሌም የመስፋቱን ሁኔታ ሉቃስ የሚተርክልን በአራት የትረካ ቡድኖች ነው፡ በመጀመሪያ፣ በሐሥ 1-2 ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥበቃና መፍሰስ፤ ሁለተኛ፣ በሐሥ 3-4 ጴጥሮስ በመቅደስ ስለ ሰበከው ስብከትና ተከትሎ ስለ መጣው ስደት፤ ሦስተኛ፣ በሐሥ 5 የሐናንያና የሰጲራ ታሪክና ተከትሎ የመጣው መከራ፤ አራተኛ ደግሞ፣ በሐሥ 6፡1-8፡4 ስለ ዲያቆናት ምርጫናተከትሎ ስለመጣው መከራ ናቸው፡፡ ሁሉን ጠቅሰን ልንዘልቅ በማንችለው መጠን፣ በሐሥ 28 ምዕራፎች ውስጥ እጅግ በርካታ ድርጊቶች ተከናውነዋል፡፡ ስለዚህ፣ ለእኛ ዓላማ ይሆነን ዘንድ፣ ስለ ውስጣዊ እድገትና ውጥረት ደግሞም ስለ ውጫዊ እድገትና ተቃውሞ ሉቃስ የጻፈበትን ቁልፍና ወሳኝ ስልት በጥቂቱ ጠቅለል አድርገን እንመለከታለን፡፡

በተምሳሊትነት መልከ፣ በኢሩሳሌም በተከናወኑ የታወቁ ተግባራት ውስጥ ውስጣዊ እድገት ይታያል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 1 የሐዋርያት መላከ፣ ይሁዳን የሚተካው ሰው ምርጫ በሐሥ 1 ውስጥ፣ በሐሥ 2 በበዓለ ሃምሳ ዕለት የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ አማኞች በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት መካፈላቸው በሐሥ 2፣ በሐሥ 2-4 ቤተክርስቲያን ያላትን ጥሪት እርስ በርስ በመካፈል ያደርጉ የነበረው መረዳዳት፣ በሐሥ 3፣4 እና 5 ውስጥ በተለይ በጴጥሮስ፣ በኢየሩሳሌም ተዓምራት መደረጉ፣ በሐሥ 5 በሃናንያና በሰጲራ ላይ በወደቀው ፍርድ እግዚአብሔርን ሰዎች መፍራታቸው፣ በሐሥ 6 የዲቁና አገልግሎት መጀመሩ ይጠቀሳሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ውስጥ ውጥረትን በተለያዩ መንገዶች እንመለከታለን፣ ይህም፡ በሐሥ 1 ሐዋርያት ሁሉም ስለሚጠቀለልበት ወቅት ሐዋርያት ያነሱትን ጥያቄ፣ በሐሥ 1 ከዐሥራሁለቱ ሐዋርያት ጋር የሚጨመረው ማን ይሁን የሚለውን ጥያቄ፣ በሐሥ 5 ስለሚለግሱት ገንዘብ ሐናንያና ሰጲራ መዋሸታቸውን እና በሐሥ 6 ከግሪክ በመጡ አይሁዶች ላይ የደረሰውን መገለል ያካትታል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ ሉቃስ በኢየሩሳሌም ስለነበረው የወንጌል አገልግሎት ያቀረበው ዘገባ ውጫዊ እድገትንና ተቃውሞንም አስከትሎ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 2 በበዓለ ሃምሳ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን 3000 ሰዎች ተጨምረው ነበር፣ በሐሥ 3-4 ሽባው ሰው በጴጥሮስ አገልግሎት ወቅት ሲፈወስ ከፈውሱ በኋላ በርካታ

ሰዎች ተጨምረው ነበር፣ በሐሥ 4 ዮሐንስና ጴጥሮስ በወህኒ ሲጣሉ የቤተክርስቲያን አባላት ቁጥር 5000 ደርሶ ነበር ደግሞም በሐሥ 6 በርካታ የአይሁድ ካህናት ወደ ቤተክርስቲያን ተጨምረው ነበር፡፡

የሆነ ሆኖ፣ ቀደም ብለን እንደተናገርነው፣ ይህ ውጫዊ እድገት ከማያምነው ዓለም ጠንካራ ተቃውሞን ያስከትል ነበር፣ ለምሳሌ፣ በሐሥ 2 በበዓለ ሃምሳ ቀን ሰዎች በሐዋርያት ላይ ማላገጣቸው፣ በሐሥ 5 ጴጥሮስና ዮሐንስ መታሰራቸውና መገረፋቸው፣ በሐሥ 5 ወንጌልን እንዳይሰብኩ መከልከላቸው፣ በሐሥ 7 የእስጢፋኖስ መሰዋት እና በሐሥ 8 ቤተክርስቲያን በስደት መበተኗ ይጠቀሳሉ፡፡

ውስጣዊ ውጥረትና ውጫዊ ስደት ያልበረታችውን (ታዳጊ የነበረችውን) ቤተክርስቲያን ተስፋ ያስቆርጣል ብለን እንገምት ይሆናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ ሆኖ የታየው እውነታ ግን ተቃራኒው ነው፡፡ የወንጌል ምስክርነት በታላቅ ብርታት ቀጠለ፣ ግስጋሴውንም ፈፅሞ ሊያስቆመው አልቻለም፡፡

# ይሁዳና ሰማርያ

በሐሥ 8፡5-9፡31 የተጻፈው ሁለተኛው የሐዋርያት ሥራ ዋና ክፍልፋይ ቤተክርስቲያን በይሁዳና በሰማርያ ባደረገችው የወንጌል ምስክርነት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የይሁዳና የሰማርያ ግዛቶች በግርድፉ በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል የተሰጠችው የተስፋይቱ ምድር ደቡባዊና ሰሜናዊ አቻ ግዛቶች ነበሩ፡፡ ኢየሱስ ራሱም ከእርገቱ አስቀድሞ በእነዚህ ግዛቶች አገልግሏል፡፡ ሉቃስ በይሁዳና በሰማርያ ላይ ያደረገው ትኩረት በሁለት ዐቢይ የታሪክ ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ እነርሱም፤ በሐሥ 8፡5-40 የፊሊጶስ አገልግሎት እና በሐሥ 9፡1-31 የጳውሎስ መለወጥ ናቸው፡፡

በአንድ በኩል፣ እነዚህ ታሪኮች ወደ ቤተክርስቲያን ውስጣዊ እድገት አትኩሮትን የሚስቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 8 አዳዲስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን በመቀጠላቸው ውስጣዊ እድገት መቀጠሉ እና በሐሥ 9 ደግሞ ሳውል ከተለወጠ በኋላ ሐዋርያ መሆኑ ይጠቀሳሉ፡፡

ሆኖም ከእነዚህ ድርጊቶች በተጓዳኝ፣ እጅ በእጅ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ውጥረት ሰፍኗል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐዋርያት ሥራ 8 ውስጥ ጥያቄዎች ተነስተዋል፣ ምክንያቱም አንዳንድ አማኞች መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ነበር፣ ሲሞን የተሰኘው ጠንቋይም በሐሥ 8 የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከሐዋርያት በገንዘብ ለመግዛት ሞክሮ ነበር፣ በሐሥ 9 ደግሞ መልሶ ቢከዳንስ በሚል አንዳንድ አማኞች ጳውሎስን ይፈሩት ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ውጫዊው እድገትና ተቃውሞም ቀጥሎ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በይሁዳና በሰማርያ የቤተክርስቲያን የቁጥር እድገትም እየጨመረ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 8 የታወቀው የመጀመሪያው አፍሪካዊ አማኝ፣ በሐሥ 8 በፊልጶስ የወንጌል አገልግሎት በርካቶች ማመናቸው እና በሐሥ 9 የሳውል መለወጥ ይጠቀሳሉ፡፡

የሆነ ሆኖ፣ ይህ እድገት ከማያምኑት ዘንድ ተቃውሞ ሳይገጥመው አልመጣም፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 9 ሳውል ከመለወጡ አስቀድሞ አማኞችን ያሳድድ ነበር፣ ከተለወጠ በኋላ ደግሞ አንዳንድ አይሁዶች በሳውል ላይ የግድያ ሴራ ጠንስሰውበት ነበር፡፡

እንደገና፣ ውስጣዊ ውጥረትና ውጫዊ ተቃውሞ የቤተክርስቲያንን እድገት ማደናቀፍ አልቻለም፡፡ ይልቁኑ፣ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ተግዳሮቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ቀጣይ ብስለትንና የቁጥር እድገትን ለማምጣት ተጠቅሞባቸዋል፡፡

# የምድር ዳርቻ

ሦስተኛው የሐዋርያት ሥራ ዐቢይ ክፍል በዚያን ዘመን ይታወቅ ከነበረው ከተስፋይቱ ምድር ድንበር ተሻግሮ፣ ወደ ምድር ዳርቻ መዝለቁን ያብራራል፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ይህንን ክፍል በበለጠ ዝርዝር የምንመለከተው ሲሆን፣ ለአሁኑ በሐሥ 9፡32-12፡25 በፊንቄ፣ በቆጵሮስና በአንጾኪያ በተገለፀው የወንጌል መስፋፋት እንጀምራለን፡፡

## ፊንቄ፣ ቆጵሮስ እና አንጾኪያ

ይህ ክፍል ወንጌል ከይሁዳና ከሰማርያ አልፎ ወደ ቅርብ የአህዛብ ምድሮች ወደ ፊንቄ፣ ቆጵሮስ እና የሶርያዋ አንጾኪያ ለመጀመሪያ ጊዜ መስፋፋቱን ይዘግባል፡፡ በዚህ የሐዋርያት ሥራ ክፍል ውስጥ፣ በሐሥ 9፡32-43 ጴጥሮስ በልዳና በኢዮጴ የሰጠውን አገልግሎት፣ በ9፡1-12፣ በቂሳርያ ከአህዛብ ወገን ለሆነው ለቆርኔሌዎስ የሰጠውን አገልግሎት፣ በ11፡13-18፣ በሶርያዋ አንጾኪያ የወንጌሉን መስፋፋት እና በ12፡1-25 ጴጥሮስ ከኢየሩሳሌም እስር ቤት በተዓምር ነፃ መውጣቱን እናነባለን፡፡

በዚህም ስፍራ የውስጥ እድገትና ውጥረት መርህ መቀጠሉ አያስገርምም፡፡ ሉቃስ በርካታ የውስጥ እድገቶችን ዘግቦልናል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 10 ውስጥ አህዛብ ወደ ቤተክርስቲያን መጡ፣ በ10-11 አህዛብና አይሁድ አማኞችን የለያዩ የአመጋገብ ገደቦች ተወገዱ፣ በሐሥ 12 ጴጥሮስ በተዓምር ከእርስ ነፃ በመውጣቱ ቤተክርስቲያን ተበረታታች፣ በሐሥ 13 ደግሞ በርናባስና ሳውል በአንጾኪያ አማኞችን ደቀመዛሙርት አደረጓቸው፡፡

እርግጥ ነው፣ ተዛማጅ የሆኑ ውጥረቶችም ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 11 በርካታ አይሁድ አህዛብን ወደሙሉ የቤተክርስቲያን ኅብረት ለማምጣት አቅማምተዋል፣ ደግሞም በርካቶቹ የብሉይ ኪዳንን የአመጋገብ ገደቦች ማላላትን ተቃውመዋል፡፡

በዚህ ክፍል በተጨማሪም፣ ሉቃስ በውጫዊ እድገትና ስደትም ላይ አፅንዖት ሰጥቶ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ ጴጥሮስ በልዳ በሰጠው የተሳካ አገልግሎት ስለ መጣው እድገት ጽፏል፣ በሐሥ 9 በሰሮናና በኢዮጴ፣ በሐሥ 10 የቆርኔሌዎስና የበርካታ አህዛብ መለወጥ፣ በሐሥ 11 በርናባስና ሌሎች የሰጡት የተሳካ የወንጌል አገልግሎት ይጠቀሳሉ፡፡

ይህ እድገት ግን ያለ ተቃውሞ አልመጣም፡፡ በሐሥ 12 ውስጥ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በሄሮድስ ተሰድዳለች፡፡ ይህም ስደት በሐስ 12 ውስጥ የያዕቆብን ሞትና የጴጥሮስን መታሰር አስከትሏል፡፡

ይህ ውጥረትና ተቃውሞ እያለም፣ የወንጌሉ ምስክርነት ሊደናቀፍ አልቻለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የቤተክርስቲያንን የወንጌል አገልግሎትና ደቀመዝሙር የማፍራቷን አገልግሎት ባርኮ ነበር፡፡ የዘር ልዩነትንና ስደትን ድል የነሳላቸው ሲሆን፣ ጴጥሮስንም በተዓምር ከእስር ነፃ አውጥቶታል፡፡ የትኛውም እንቅፋት በጎዳናው ላይ ቢወረወርበትም፣ ወንጌል ግስጋሴው አልተገታም፡፡

## ቆጵሮስ፣ ፍርግያ እና ገላትያ

በሐሥ 13፡1-15፡35፣ ሉቃስ ወደ አራተኛው ዋና ክፍል ይሸጋገራል፡፡ ያም በቆጵሮስ፣ በፍርግያና በገላትያ የወንጌል መስፋፋት ነው፡፡ በዚህ ክፍል፣ ወንጌል ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከሰማርያ ተሻግሮ ወደ ምሥራቃዊው የትንሿ እስያ ክፍል ይሸጋገራል፡፡ ይህ የሐዋርያት ሥራ ክፍል በሁለት ዋና ክፍሎች

ይከፈላል፡፡ እነርሱም በሐሥ 13፡1-14፡28 የሚገኘው የጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ እና በሐሥ 15፡1-35 የሚገኘው የኢየሩሳሌም ጉባኤ ናቸው፡፡

ሉቃስ ስልቱን በመጠበቅ፣ በዚህም ክፍል ውስጥ የውስጥ እድገትና ውጥረትን ንድፍ ያንፀባርቃል፡፡ በሐሥ 13፣ ኤልማስ የተሰኘውን ጠንቋይ በማሳወር፣ በተገለጠው የጳውሎስ ሐዋርያዊ የተዓምራት ስጦታ፣ በሐሥ 14 የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትን ጳውሎስ በማበርታታቱ፣ በሐሥ 15 ከአህዛብ ወገን ወደ ክርስቶስ የመጡትን እንዲገረዙ ላለማስገደድ የኢየሩሳሌም ጉባኤ ባስተላለፈው ውሳኔ፣ ውስጣዊ እድገት መታየቱን ያመለክታል፡፡

ሉቃስ በተጨማሪ በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም ከአህዛብ አማኞች ጋር የተያያዙ ተዛምዷዊ ችግሮችን አስመልክቶ ሲፅፍ፣ ስለ ውስጣዊ ውጥረት ጠቅሷል፡፡ ውጥረቱም በሐሥ 15 እንደተጠቀሰው፣ መገረዝንና የአይሁዳውያን ባህላዊ አመጋገብን ከመጠበቅ አንፃር በአይሁድና በአህዛብ አማኞች መካከል የተቀሰቀሰ ነበር፡፡

በሐሥ 14 ተመዝግቦ እንደምናገኘው፣ ከውጫዊ እድገትና ተቃውሞ አንፃር ሉቃስ በርካታ ጉዳዮችን ይጠቅሳል፣ ይህም በጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ የተገኘውን የቁጥር እድገት የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ይህ እድገት በጠንካራ ተቃውሞም የታጀበ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 14 እንደተገለጠው ጳውሎስና በርናባስ በተለይ በልስጥራ፣ በኢቆንዮንና በአንፆኪያ ከማያምኑት አይሁድ ተደጋጋሚ ተቃውሞ ደርሶባቸው ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ፣ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን ወደፊት እንድትገፋ ከማድረጉ ባሻገር ከህዝቡ መንገድም ላይ እንቅፋትን ያስወግድ ነበር፡፡ ስለዚህም ማንም ሊያቆመው የማይችለው ወንጌል የእግዚአብሔርን ዓላማዎች መፈፀሙን ቀጥሏል፡፡

## እስያ መቄዶኒያ እና አካይያ

ከሐሥ 15፡36-21፥16 የሚዘልቀው አምስተኛው የሐዋርያት ሥራ ዐቢይ ክፍል፣ የወንጌሉ ምስክርነት የሮሜ ግዛቶች ወደሆኑት ወደ እስያ፣ መቄዶኒያ እና አካይያ መዛመቱን የሚተርክ ነው፡፡ ይህ የሐዋርያት ስራ ክፍል የሚያተኩረው በጳውሎስ ሁለተኛና ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ ነበር፡፡ በዚያም ወቅት ጳውሎስ ቀድሞ እንዳደረገው ሁሉ፣ በትንሿ እስያ ምሥራቃዊ ክፍል ተጉዞ፣ ከዚያም ወደ ምዕራባዊው የትንሿ እስያ ክፍል ያቀና ሲሆን በኤዥያን ባህርም አቋርጦ የዘመናዊቷ የግሪክ ግዛት በሆኑት መቄዶኒያና አካይያ በሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች ዘልቋል፡፡

የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ በሐሥ 15፡36-18፡22 ውስጥ የተመዘገበ ሲሆን፣ ሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ ደግሞ በሐሥ 18፡23-21፡16 ተመዝግቧል፡፡ በአሁኑ ወቅት በደንብ ተዋውቀናል ብለን በምናስበው ንድፍ መሠረት፣ እነዚህ ምዕራፎች በውስጣዊ እድገትና ውጥረት መካከል ስላለው ግንኙነት አፅንዖት ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ስፍራ የውስጣዊ እድገትን በርካታ ተምሳሊቶች እናገኛለን፡፡ እነርሱም፡ በሐሥ 15 የምናገኘው የአይሁድ ቤክርስቲያናት ለአህዛብ ክርስቲያኖች ያሳዩት ተቀርቋሪነት፣ በሐሥ 18 የምናገኘው አቂላና ጵርስቅላ ለአጵሎስ የሰጡት የማበረታቻ ትምህርት፣ በሐሥ 19 የምናገኘው የመጥምቁ ዮሐንስን ፈለግ ለሚከተሉ ደቀመዛሙርት ጳውሎስ የሰጠው አገልግሎት፣ በሐሥ 19 የምናገኘው ጳውሎስ በኤፌሶን ምኩራቦች እና በጢራኖስ የደቀመዝሙርነት ትምህርት ቤት የሰጠው የረጅም ጊዜ አገልግሎት ናቸው፡፡

እነዚህን ውስጣዊ እድገቶች በርካታ ውጥረቶች ያጀቧቸው መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 15 ጳውሎስና በርናባስ በማርቆስ ምክንያት ሊስማሙ ባለመቻላቸው መለያየታቸው፣ በሐሥ 21 ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የሚያደርገውን ጉዞ አጋቦስ የተባለው ነቢይና ቤተክርስቲያን መቃወማቸው፣ በሐሥ 20 ክፉ ሃሳብ ካላቸው መሪዎች ቤተክርስቲያንን ስለ መጠበቅ ጳውሎስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ይጠቀሳሉ፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ስለ ውጫዊ እድገትና ተቃውሞም እናነባለን፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 15-21 ውስጥ በተመዘገበው የጳውሎስ ሁለተኛና ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ አማካይነት የዳኑ ሰዎችና በተመሠረቱት አብያተክርስቲያናት ውስጥ የተመዘገቡት የሰዎች መዳንና የቁጥር እድገት፡፡ ይህንኑ ተከትሎ የመጣውና በሐሥ 17-21 የምናገኘው ተቃውሞ፣ ጳውሎስን ለመግደል የተነሳው ሁከት፣ በሐሥ 17-20 እንደተጠቀሰው ጳውሎስን ከከተማ ወደ ከተማ የሚከታተሉት የአይሁድ ቀናተኞች፣ በእርሱ ላይ የሚያስነሱት ህዝባዊ ተቃውሞ ይጠቀሳሉ፡፡ ወንጌል በመላው ዓለም በስኬት እየሰፋ መሄዱን ሉቃስ ደግሞ ያሳየናል፡፡ ውስጣዊ ውጥረት እና ውጫዊ ተቃውሞ የዘወትር ችግሮች ቢሆኑም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚገሰግሰውን የወንጌል እድገት ሊያቆሙት ግን አልቻሉም፡፡

## ሮም

በመጨረሻ፣ በሐሥ 21፡17-28፡31 ውስጥ የሉቃስ ትረካ የመጨረሻው ክፍል በሮም በተሰጠው የወንጌል ምስክርነት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ይህ ክፍል ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገው ጉዞ፣ በዚያም በመያዙ፣ በመታሰሩና ወደ ሮም በመላኩ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ክፍል በግርድፉ በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ እነርሱም፡ በሐሥ 21፡17-23፡11 ጳውሎስ በኢሩሳሌም የሰጠው የመጨረሻ ምስክርነት፣ በሐሥ 23፡12-26፡32 የጳውሎስ መታሰር፣ በሐሥ 27፡1-28፡14 ወደ ሮም ያደረገው ፈታኝ ጉዞ እና በመጨረሻ፣ በሐሥ 28፡15-31 በሮም የሰጠው ምስክርነት ናቸው፡፡

በዚህኛውም ክፍል አይቀሬ ነው ብለን እንደምንጠብቀው፣ እነዚህም ምዕራፎች የውስጣዊ እድገትንና ውጥረትን ንድፍ ይከተላሉ፡፡ የውስጣዊ እድገት መገለጫ የሚሆኑ በርካታ ማስረጃዎችን እናገኛለን፣ ከእነዚህም፡ በሐሥ 20-21 የተመዘገበው የአህዛብ ቤተክርስቲያናት በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ድሆች የላኩት የገንዘብ ስጦታ፣ በሐሥ 21 የምናነብበውና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁድ አማኞች በርካታ አህዛብ ወደ እምነት መምጣታቸውን ሲሰሙ የተሰማቸው ደስታ እና በሐሥ 22 ጳውሎስና ሌሎች ወንጌልን ለማዳረስ እስከሞት ድረስ መከራን ለመቀበል መፍቀዳቸው ይጠቀሳሉ፡፡

ሆኖም ይህ ውስጣዊ እድገት በውጥረት የታጀበም ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ አይሁድ አማኞች ወጎቻቸውን ችላ እንዲሉ ጳውሎስ ያስተምራል የሚለው ጉምጉምታ በሐሥ 21 ውስጥ እና በዚያው ምዕራፍ የጳውሎስ መገኘት በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ ያስነሳው ተከታታይ ውጥረት ይጠቀሳሉ፡፡

እንዲሁም፣ የውጫዊ እድገትንና ተቃውሞን ንድፍም እናገኛለን፡፡ በዚህ ወቅት ቤተክርስቲያን ያሳየቻቸውን ፈጣን ግስጋሴዎች ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በእርስ ቤት ሳለ እንኳን፣ ወንጌልን በነፃነት መስበኩ በሐሥ 28 ውስጥ፣ ጳውሎስ ለበርካታ ከፍተኛ ባለስልጣናት የወንጌልን መልእክት ማቅረቡ በሐሥ23፣24፣25፣26፣28 ውስጥ፣ በመላጥያ ደሴት ጳውሎስ የሰጠው አጓጊ አገልግሎት በሐሥ 28 ውስጥ፣ በሮም ውስጥ ያለምንም እንቅፋት መስበክ መቻሉ በሐሥ 28 ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡ ሆኖም ይህንን እድገት ተከትሎ የመጣውንም ጠንካራ ተቃውሞ ሉቃስ የዘገበ ሲሆን፣ ይህም በሐሥ 24 በማያምኑ አይሁድ በጳውሎስ ላይ የተመሠረተውን የሃሰት ክስ ያካትታል፡፡ በሐሥ 24፣ ጳውሎስ ተይዞ በሮሜ አስተዳደር የአራት ዓመት እሥራት ተበይኖበታል፣ በሐስ 22-23 በርካታ አይሁድ ጳውሎስን ለመግደል አሲረዋል፣ በሐሥ 28 ጳውሎስ ታስሯል፡፡

እያንዳንዱ ዐቢይ ክፍል በታማኝነት የቀረበው የወንጌል ምስክርነት ከንቱ አለመቅረቱን ያረጋግጣል፡፡ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ተነስቶ ወደ ሮማውያን ግዛት ዋና ከተማ እንዲደርስ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን አበርትቷታል፡፡ ቤተክርስቲያን ባለፈችባቸው የውስጥና የውጭ ተግዳሮቶች በመጽናት ማንም ሊያደናቅፈው የማይችለውን ወንጌል ወደ ምድር ዳርቻ ሁሉ በማድረስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስታሰፋ ወደ መንፈሳዊ ብስለትና የቁጥር እድገት ተሸጋግራለች፡፡

# 4. በእኛ ዘመን የሚኖረው ተዛምዶ

የሐዋርያት ሥራን የአጻጻፍ ስልት ከተመለከትን ወደ አራተኛውና በእኛ ዘመን የሚኖረውን ተዛምዶ ወደ ምንመለከትበት ርዕስ እንሸጋገር፡፡ የሐዋርያት ሥራን እውነታዎች በእኛ ዘመን በምናዛምድበት ወቅት ልናተኩርባቸው የሚገቡ ጥቂት ዐበይት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ይህንን ርዕስ ለመዳሰስ፣ በመጀመሪያ፣ አንዳንድ ባህርያቱን በአትኩሮት በማየት በሐዋርያት ሥራ ስነ-ጽሑፋዊ ባህርይ ላይ እናተኩራለን፡፡ ሁለተኛ፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመንና በእኛ ዘመን መካከል በነበሩት የመሃል ክፍተቶች እና በእኛ ዘመን ተዛምዶ ላይ ስለፈጠሩት ተፅዕኖ እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመንና በእኛ ዘመን መካከል ዛሬም ቀጥለው ያሉ አንዳንድ ወሳኝ ጉዳዮችን በማረጋገጥ የሐዋርያት ሥራ ቀደምት ትርጉም በእኛ ሕይወት ተግባራዊ የሚሆንበትን እንዳስሳለን፡፡ በሐዋርያት ሥራ ስነ-ጽሑፋዊ ባህርይ እንጀምር፡፡

## ስነ-ጽሑፋዊ ባህርይ

የተለያዩ የስነ-ጽሁፍ ዓይነቶች ሃሳቦቻቸውን በተለያዩ መንገዶች ያስተላልፋሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ የስነ-ጽሑፍ ዓይነቶች አሉ፡፡ ታሪካዊ ትረካዎች፣ ግጥሞች፣ ንግግሮች፣ ምሳሌዎች፣ ቅኔዎች፣ ህግ፣ እና ሌሎችም አሉ፡፡ እያንዳንዳቸውም በተለያዩ መንገዶች መልእክታቸውን ያስተላልፋሉ፡፡ የሐዋርያት ሥራ ሃላፊነት እንደሚሰማው ሰው ለመረዳት ከፈለግን፣ ምን ዓይነት ስነ-ጽሑፍ እንደሆነ እና የዚያ ዓይነት ስነ-ጽሑፍ ሃሳቦቹን እንዴት እንደሚያስተላልፍ ማስተዋል ይገባናል፡፡

ከስነ-ጽሑፍ አንፃር ስለ ሐዋርያት ሥራ የምንናገረው ብዙ ነገር ቢኖረንም፣ ወሳኝ በሆኑት ሦስት ባሕርያቱ ላይ ብቻ እንድናተኩር ጊዜ ይወስነናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ሉቃስ የሚዘግበውን ነገር በጥንቃቄ ይመርጣል፡፡ ሁለተኛ፣ የሐዋርያት ሥራ አጫጭር ትረካዎችን እንዲይዝ አድርጓል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በርካታ ትምህርቶቹን በተዘዋዋሪ አቅርቧቸዋል፡፡  እስኪ በመጀመሪያ በሐዋርያት ሥራ የተቀመጡት ታሪኮች በጥንቃቄ የተመረጡ መሆኑን እንመልከት፡፡

### በጥንቃቄ የተመረጡ/የተመጠኑ

እያንዳንዱ የታሪክ ጸሐፊ ጠንቃቃ ምርጫ ያደርጋል፡፡ አንድ ሰው በርካታ ዝርዝር ሪፖርቶችን ሊሰጥባቸው የሚችላቸው እውነታዎች፣ ህዝብ፣ እና ክንውኖች በዓለም ላይ ይገኛሉ፡፡ በሐዋርያት ሥራ የተመዘገበው ታሪክ ከኢየሱስ እርገት ጳውሎስ በሮም እስከታሰረበት ዘመን ድረስ ያለውን ሦስት ወይም አራት ዐሥርት ዓመታት ይሸፍናል፡፡ በዚህ ወቅት በቤተክርስቲያን ውስጥ አስገራሚም አስደንጋጭም ጉልህ ድርጊቶች ለቁጥር በሚያታክት መጠን ተከናውነዋል፡፡ ሉቃስ ግን የተመጠኑ 28 ምዕራፎችን ብቻ ጽፏል፡፡ ስለዚህ፣ ሊነገር ከሚገባው እጅግ በጣም ትንሿን እንደዘገበ እናውቃለን፡፡ የትኛውን ድርጊት እንደሚያካትት እንዴት ወሰነ?  የትኛውንስ መተው እንዳለበት እንዴት ወሰነ? በሐዋርያት አማካይነት የተከናወነውን የኢየሱስን ሥራ ለመረዳት ወሳኝ የሆኑትን የታሪክ አንጓዎች እንዲመርጥ እና ከሐዋርያት አስተምህሮዎች ማእከላዊ የሆኑትን ጥቂቶቹን አንባቢዎቹ የራሳቸው እንዲያደርጓቸው ለማመልከት ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ ተነድቷል፡፡

ስለዚህ፣ በዘመናኛው ዓለም የሐዋርያትን ሥራ የምናዛምድበትን መንገድ ለመፈለግ፣ ሁለት ነገሮችን ማድረግ ይገባናል፡፡ በአንድ በኩል፣ በዚህ የቤተክርስቲያን ዘመን ስለ ተከናወነው ድርጊት እኛ ለማወቅ የምንፈልገውን ሁሉ ሉቃስ ዘግቧል የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ማስወገድ ይገባናል፡፡ ምላሽ ሳይሰጥባቸው ያለፋቸው በርካታ ጥያቄዎች አሉ፣ ስለዚህ ከሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለእኛ ዘመን የሚያስፈልጉንን መልሶች ሁሉ የማሰስን ጥረት ማቆም አለብን፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ታሪክ ሉቃስ ባለ ሁለት መንታ አላማዎቹን እንዲያሳካ ሊያግዙት የተቀመጡ እንደሆኑ ማስታወስ ይገባናል፡፡ ስለዚህ፣ በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን ነገር ልናነብብ የሚገባን ሉቃስ እነዚህን ግቦቹን ለመምታት እንዴት እንደሚያግዙት ነው፡፡ ስለዚህ ዘወትር፡ ስለ ቀደመችው ቤተክርስቲያን ይህ ምን ያስተምረናል? የትኛውንስ አስተምህሮ የራሴ እንዳደርገው ያበረታታኛል የሚለውን ጥያቄ ልንጠይቅ ይገባናል፡፡

# አጫጭር ትረካ

በጥንቃቄ ምርጫውን ያደረገ ከመሆኑ ባሻገር፣ የሐዋርያት ሥራ አጫጭር ትረካዎችን ያዘለ ነው፡፡ ያም ማለት፣ የሐዋርያት ሥራ እርስ በርስ የተያያዙ አጫጭር ታሪኮችና ድርጊቶች ስብስብ ነው ማለት ነው፡፡ የሐዋርያትን ሥራ ስናነብብ፣ እያንዳንዱ ክፍልፋይ ትረካ የሉቃስ አጠቃላይ ስልትና መልእክት ክፍል መሆኑን ማስታወስ ይገባናል፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለተገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ቴዎፍሎስን ለማስተማር የያዘውን ጥቅል ተልዕኮ ለማሳካት እያንዳንዳቸው በአንድ መንገድ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ፣ ይህ ትልቅ ምስል በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለሚገኙት አጫጭር ትረካዎች የኋላ ደጀንና አውድ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ሆኖም እያንዳንዱ ትረካ የተለየ ነገር አለው፡፡ እያንዳንዳቸው የሚመሠርቱት ጭብጥ አላቸው፣ ያም በክርስቶስ የተገለጠውን የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ቤተክርስቲያን ያስፋፋችበትን መንገድ የሚያስተምሩበትን የራሳቸውን ዝርዝር ያቀርባሉ፡፡ ይህም ማለት የሐዋርያት ሥራን ስናነብብ፣ በሉቃስ መሪ ዓላማ ላይ የምናደርገው ትኩረት በዝርዝር ነጥቦቹ ላይ የሚመሠርተውን ጭብጥ ጥላ እንዲያጠላበት መፍቀድ የለብንም፡፡ ስለዚህ ለትልቁም ለትናንሹም ስዕሎች ትኩረት በመስጠት፣ እያንዳንዱ ትረካ ለታላቁ ግብ እንዴት አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ፣ ደግሞም እያንዳንዱ ትረካ የግቡን ዝርዝሮች ለማብራራት እንዴት እንደሚያግዝ ልንረዳ ይገባል፡፡

ጥንቃቄ ከሞላበት ምርጫ እና ከአጫጭር ትረካ በተጨማሪ፣ የሐዋርያት ሥራ የትረካ ቅርፁ ትምህርቱን የሚያስተላልፍበት ስነ-ጽሁፋዊ ዓይነት ተዘዋዋሪ መሆኑን ያሳያል፡፡

# በተዘዋዋሪ

በስፋት ስንናገር፣ በአዲስ ኪዳን ሁለት ዓይነት ስነ-ጽሁፍ አለ፡፡ ትረካዊ ንግግር እና ሙግታዊ ንግግሮች ናቸው፡፡ ሙግታዊ ንግግሮቹ አንድን ዓይነት ክርክር የሚገልፅ ስነ-ጽሑፍ ሲሆን፣ ያም በመጽሐፉ ውስጥ ያለ ገፀ-ባህርይ ሲናገር፣ ወይም ጸሐፊው ለተደራሲያኑ በቀጥታ ሲናገር የሚታይበት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች በተቀዳሚነት የያዙት ሙግታዊ ንግግሮችን ሲሆን ጳውሎስን የመሳሰሉ ጸሐፍት ለደብዳቤዎቹ ተቀባዮች በቀጥታ የሚናገሩበት ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ አንዳንድ ደብዳቤዎች ቁርጥራጭ ትረካዎች፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወቅታዊ ዝማሬዎችን ወይም ምሳሌዎችን ያካትታሉ፡፡ በአብዛኛው ግን ሙግታዊ ንግግሮችን የያዙ ናቸው፡፡ ስለ ሙግታዊ ንግግሮች በዚህ ስፍራ ማስተላለፍ የፈለግነው መልእክታቸውን በቀጥታና በግልፅነት ሚያስተላልፉ መሆኑን ነው፡፡ ጳውሎስ ደብዳቤ የሚጽፈው አንባቢዎቹ እንዲያስቡ ወይም እንዲያደርጉ ስለሚፈለግባቸው አንድ ነገር ለመንገር ሲሆን፣ እርሱ የሚፈልገውን ነገር ይነግራቸዋል፡፡

በሌላ በኩል፣ ትረካዊ ንግግሮች በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ገዢ የሆኑ የስነ-ጽሁፍ ዓይነቶች ሲሆኑ፣ ከሁሉም በጣም ወሳኝ በሆነ መንገድ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተገለጡት ትምህርቶች ተንጸባርቋል፡፡ ትረካዊ ንግግር ትሪክ የሚተርክ ይሆንና ቀጥተኛነቱ ሳሳ ባለ መልኩ ትምህርት ያለበት ይሆናል፡፡ በእርግጠኝነት፣ በእነዚህ መጻሕፍቶች ውስጥ ሙግታዊ ንግግሮችም ይገኛሉ፣ በተቀዳሚነትም የሚገኙት በውሱን ገጸ-ባህርያት

ንግግር ውስጥ ነው፡፡ የወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ ዐቢይ የስነ-ጽሑፍ ባሕርይ ትረካ ነው፡፡ ትምህርቶቹን ቀጥተኛና ግልፅ ወደማድረጉ ከሚያዘነብለው ከሙግታዊ ንግግር ተቃራኒ በሆነ መንገድ፣ ትረካዊ ንግግር ትምህርት የሚሰጠው አንባቢው ትምህርቱን ራሱ በሚረዳበት በተዘዋዋሪ መንገድ ነው፡፡ ትረካዎች አንባቢዎቻቸውን የሚሞግቱት በቀጥተኛ መመሪያዎች ሳይሆን፣ ሰወር ባለ መንገድ ነው፡፡ አንባቢዎቹ ከገጸ-ባህርያቱ አስተሳሰብ፣ ድርጊትና ቃሎች ውስጥ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚሰኘውን በመለየት የራሳቸው እንዲያደርጉ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ ከሆኑት ደግሞ ራሳቸውን እነዲያርቁ ተደርገው የሚቀረፁ ናቸው፡፡

እስኪ በዚህ መንገድ አስቡት፡፡ የሐዋርያት ሥራ የመሳሰሉ ትረካዎች፣ አብዛኛ ክፍላቸው እውነታዎችን የሚገልፁ ናቸው፡፡ ይህ ሆነ፣ ያ ሆነ፣ ከዚያም ሌላኛው ደግሞ ሆነ የሚሉ ናቸው፡፡ በሜዳዊ ገፅታቸው፣ የአንዳንድ ድርጊቶች ዘገባዎች ናቸው፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው፣ በትረካው ውስጥ ስላካተታቸው ወሳኝ ውቅረ-ነገሮች አልፎ አልፎ ግልፅ አስተያየት በመስጠት ዘግቧል፡፡ በአብዛኛዎቹ  ክፍሎች ግን፣ ድርጊቶችን ወይንም እውነታዎችን ያለምንም አስተያየት ያስቀምጣቸዋል፡፡ የሆነ-ሆኖ፣ እውነታው ትረካዎቹ የተጻፉት ድርጊቶችን ለመዘገብ ያህል ብቻ አለመሆኑ ነው፡፡ ትምህርት የመስጠት ውስጣዊ መሻትም ነበረው፣ እናም ትረካዎቹ እነዚያን ሃሳቦች በግልፅ እንዲያስተላልፉለት ተጠቅሞባቸዋል፡፡

ይህንን ሃሳብ እኔው በገጠመኝ ታሪክ ላብራራላችሁ፡፡ ሴት ልጄ ታዳጊ ሳለች፣ ከእራት በፊት ጣፋጭ እንዳትመገብ ተነገራት፡፡ አንድ ቀን ግን ከንፈሮቿ በጣፋጭ ምግብ ቅሪቶች ተነክረው ወደ ገበታው መጣች፡፡ እኔም ጣፋጭ በልታ እንደሆን ጠየቅኋት፣ እርሷም ዐይኖቿን በክህደት እያጉረጠረጠች አባዬ “እኔ ምንም ጣፋጭ አልቀመስኩም” አለች፡፡

እንደ ወላጅ፣ ይህንን ሁኔታ ልጋጠመው የምችልበት ሁለት መንገዶች አሉኝ፡፡ ሙግታዊ በሆነ ንግግር ጉዳዩን በግልፅና በቀጥተኛነት መጋፈጥ፡፡ “እውነቱን አልነገርሽኝም፡፡ የታፋጩን ነገር ቅሪት አየዋለሁ! ችግር ውስጥ ነሽ!” ማለት እችላለሁ፡፡ ስውርና ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ፣ መግለጽ የምችልበት ትረካዊ ምርጫም አለኝ፡፡ ትንሿን ልጄን በጭኔ ላይ ቁጭ አድርጌ፣ አንድ ታሪክ ልንገርሽ፡፡ “ከእለታት አንድ ቀን፣ የተመረጠ ልብሷን ለብሳ እንዳትጫወት የተነገራት ትንሽ ልጅ ነበረች፡፡ ሆኖም ልብሷል ለብሳ ተጫወተችና በጣም ቆሸሸ፡፡ ስለ ትንሿ ልጅ ድርጊት ምን ታስቢያለሽ?”

ይህንን የመሰለው ትረካዊ የአጻጻፍ ስልት በተቀዳሚነት የሚያገለግለው በሰዋራነት ደረጃ ነው፡፡ “ትንሿ ልጅ አለመታዘዟ መጥፎ አይደለምን?” በማለት ልጅቷን መጋበዝ ይቻላል፡፡ የትረካ ውበቱና ኃይሉ እነዚህን የመሳሰሉ ሃሳቦች ሰውር በሆነ መንገድ ማስተላለፍ መቻሉ ነው፡፡ ትረካ ሰዋራ በሆነ መንገድ ከተቀመጠ፣ አድማጩ በትረካው ውስጥ እንዲገባበት የማድረግ አቅም አለው፡፡ አድማጩ ተቃዋሚ በሆነ መንገድ ከመቆም ይልቅ እርሱ ራሱም እንዲገባበት ያግዘዋል፡፡ አድማጩ ይበልጥ ተማሪ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡

ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ 70% ያህሉ በትረካ መልክ የቀረበ ነው፡፡ በመጽሐፉ አብዛኛ ክፍል፣ ሉቃስ ለአድማጮቹ ሲናገር “በቀደመችው ቤተክርስቲያን ስለተከናወነው የእግዚአብሔር ሥራ ታሪክ ልንገራችሁ” እያለ ነበር፡፡ እርግጥ ነው፣ የነገራቸው ታሪክ ፍፁም እውነት ነበር፡፡ ወደ እውነተኛው ጭብጥ ታሪክ ወደተመዘገበበት ዓለም ውስጥ እየጋበዛቸው ነው፡፡ ይህን ታሪክ የሚያቀርብላቸው ግን በታሪክ መልክ ሲሆን ምክንያቱም እርሱ ከዘገባቸው እውነታዎች ውስጥ ማጠቃለያውን አንባቢዎቹ ራሳቸው እንዲያወጡ ስለሚፈልግ ነው፡፡ ስለዚህ፣ የሐዋርያት ሥራን ስናነብብ፣ እነዚህን ስውር አስተምህሮዎች ማሰሳችን ወሳኝነት አለው፡፡

እርግጥ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎችን የምንመዝንበትና ከእኛ ሕይወት ጋር የምናዛምድበት አንዱ መንገድ ለተከናወኑት ድርጊቶች እግዚአብሔር እንዴት ምላሽ እንደሰጠ መመልከት ነው፡፡ ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ፣ የእርሱ ቃሎችና ድርጊቶች ፈፅሞ አይሻሩም፡፡ በውጤቱም፣ በሐዋርያት ሥራ ከተከናወኑት ድርጊቶች እግዚአብሔር ያጸደቃቸውንና የባረካቸውን ደግሞም ውድቅ ያደረጋቸውንና የረገማቸውን ዘወትር ልብ ማለት ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር የባረካቸው ነገሮች መልካም ሊሆኑ የተገባ ሲሆን፣ ደግሞም ውድቅ ያደረጋቸውና የረገማቸው ክፉዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ የሐዋርያት ሥራን ስናነብብ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙትን እምነቶች፣ ዝንባሌዎች እና ባህርያት ልንመስላቸው ሲገባ፣ እርሱን የሚቃወሙትን ደግሞ ልናስወግዳቸው ይገባናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ሉቃስ እጅግ አብዝቶ የሚደገፈው በቀደምት የቤተክርስቲያን እውቅ መሪዎች አመለካከት ላይ በመሆኑ ምክንያት፣ የሉቃስን አስተምህሮ የምንመለከትበት ሌላኛው አስተማማኝ መንገድ፣ ሉቃስ ያቀረበልንን ተምሳሊቶች መመልከት ነው፡፡ ሐዋርያትን፣ ነቢያትን እና ሌሎች የታመኑ የቤተክርስቲያን መሪዎችን የመሳሰሉ የታመኑ ሰዎች አንድ ነገር ካደረጉ ወይም ከተናገሩ፣ አዘውትረን ከእነርሱ ጋር የምንስማማ መሆናችንን ማመልከት ይገባናል፡፡ ድርጊቶቻቸው ተገቢ ሲሆኑ፣ ምስክርነታቸውም እውነት ነው፡፡ ስለዚህም እኛ ከልባችን ለጥሪው ምላሽ ልንሰጥ እና ባህርያችንንና አስተሳሰባችንን በእነርሱ ተምሳሊትነት ልንቃኝ ይገባናል፡፡

ደግሞም ለተቃራኒውም ምላሻችን እንደዚያው ሊሆን ይገባል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙ ባህርያት በሐዋርያትና በቤተክርስቲያን የተወገዙ ከሆነ፣ ድርጊታቸው ክፉ መሆኑን ልንረዳ እና ምሳሌነታቸውንም ላለመከተል መወሰን ይገባናል፡፡ እንግዲህ፣ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ሊያመለክተን የፈለገው እነዚህን እንድምታዎች ብቻ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ እነዚህ ግን፣ እኛ የዘመኑ አንባቢዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎች ትክክለኛ ድምዳሜዎችን እንዴት መመሥረት እንደምንችል ማወቅ የምንጀምርበትን ጠንካራ መሠረት ይሰጡናል፡፡

ይህንን የሐዋርያት ሥራ ስነ-ጽሑፋዊ ባህርይ በልቡናችን ይዘን፣ የሐዋርያት ሥራን ከማዛመድ አንፃር ተፅዕኖ ወደ ሚያሳድሩብን የተቋረጡ ነገሮች ልንሸጋገር ይገባናል፡፡

## የተቋረጡ

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛም የተጻፈ ቢሆንም፣ በቀጥታ ለእኛ እንዳልተጻፈ ዘወትር ልናስታውስ ይገባል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ተቀባዮች ቴዎፍሎስና የመጀመሪያው ምዕተ ዓመተ-ምህረት ህዝብ ናቸው፡፡ ስለዚህ፣ በአንድ ወገን የሉቃስን መጽሐፍ ስናነብብ በእነርሱ ትከሻ ላይ አሻግረን ነው፡፡ ስለዚህ ለእነርሱ ከተናገራቸው ነገር ውጪ ለእኛ እነደሚናገር ካሰብን ሊቃስን እየሰማነው አይደለም፡፡ ስለዚህ፣ ስለዚህ በሐዋርያት ሥራ ከተቀመጡት ትምህርቶች መካከል ጥቂቶቹ ለቴዎፍሎስና ለተቀሩት የሉቃስ ተደራሲያን ከነበራቸው ተዛምዶ ለየት ያለ ተዛምዶ እንደሚኖራቸው ልንጠብቅ ይገባናል፡፡ ይህንን ልዩነት ሳናስተውል በቅዱሳት መጻህፍት የምናገኘውን በቀጥታ የምናዛምደው ከሆነ፣ ደግመን ደጋግመን የእግዚአብሔርን ቃል አሰቃቂ በሆነ መንገድ በተሳሳተ ሁኔታ እናዛምደዋለን፡፡

በሉቃስ ዓለምና በእኛ መካከል ያሉትን ያልቀጠሉ/የተቋረጡ ነገሮች በሁለት መንገዶች እናጠቃልላቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ እነርሱ ከኖሩበት ዘመን በተለየ ዘመን መኖራችን ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ከመጀመሪው ምዕተ-ዓመት ጀምሮ ዓለም እየተለወጠች ነው፡፡ ስለዚህም፣ የተለዩ ሁኔታዎች ዙሪያችንን አሉ፣ ሉቃስ መጀመሪያ ሲጽፍ ከነበረው የተለየ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ነን፡፡ በመጀመሪያ የሐዋርያትን ሥራ መጀመሪያ ከተቀበሉት በተሌ ዘመን የምንኖር የመሆናችንን እውነታ እንመለከታለን፡፡

## የተለያየ ዘመን

እኛ የምንኖርበት ዘመን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ከነበረበት የእድገት ደረጃ እጅግ በላቀ የእድገት እርከን ላይ የደረሰበት የተለየ ዘመን ነው:: ይህም እውነታ በሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያ ተቀባዮችና በእኛ መካከል ያልቀጠሉና የተቋረጡ ነገሮች መኖራቸውን በተወሰነ እርከን ያሳየናል::

የሐዋርያት ሥራ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበሩ የክርስቶስ ባለሥልጣን ሐዋርያት ላይ ያተኮረ እንደሆነ ማስታወሱ ጠቃሚ ነው:: በሐዋርያት የተከናወኑት የእግዚአብሔር ሥራዎች በመቤዠት ታሪክ ውስጥ ለዚያ ወቅትእና ስፍራ የተለዩ ነበሩ፤ ድርጊቶቹ ፈርቀዳጅ፣ መሠረታዊ ክንዋኔዎች ሲሆኑ ዳግመኛ ሊከሰቱ የማይችሉ ናቸው:: አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት፣ የዚያን ዘመን ሐዋርያት ኑባሬ ልዩ ነበር:: ወደኋላ በምንመለከተው ትምህርት እንደምናነሳው፣ ሌላ ሐዋርያ ሊኖር አይችልም:: አንዱ ነገር፣ አንድ ሰው ለሐዋርያ ቢሮ ብቁ ለመሆን፣ ከሞት የተነሣውን ጌታ ሊያይ ይገባዋል:: ሌላው ደግሞ፣ በእግዚአብሔር በራሱ ለሐዋርያነት አገልግሎት ሊሾም ይገባዋል:: ስለዚህ፣ የቤተክርስቲያን መሪዎቻችንን እንድናከብር የሐዋርያት ሥራ ያስተምረናል ማለቱ አግባብነት ቢኖረውም፣ በእኛ ዘመን በሕይወት የሚኖሩ ሐዋርያት ግን የሉንም:: ልናደርገው የሚገባው የተሻለ ነገር ቢኖር በአዲስ ኪዳን ለሰፈረው ትምህርታቸው ራሳችንን ማስገዛት ነው::

የሚሳዝነው ግን፣ በርካታ ክርስቲያናዊ ቡድኖች የሐዋርያት ሥራን የሚመለከቱት በየዘመናቱ አንዲቷም ሳትዛነፍ ሊኖር የሚገባውን ክርስቲያናዊ አኗኗር ተምሳሊት አድርገው መሆኑ ነው:: ለምሳሌ፣ የሐሥ 2፡1-4 መንፈስ ቅዱስ ድራማዊና ተዓምራዊ በሆነ መንገድ በበዓለ ሃምሳ ቀን እንደፈሰሰ፣ የተቀበሉትም ሰዎች ወንጌልን በተለያዩ ቋንቋዎች ማወጅ እንደጀመሩ ያስተምረናል:: ይህም ሐዋርያትንና የመጀመሪያውን ዘመን ክርስቲያኖች ለክርስቶስ አገልግሎት በኃይል ለማስታጠቅ በመጀመሪያ ላይ የፈሰሰው ዓይነት መፍሰስ ነው:: ተመሳሳዮቹም ሁኔታዎች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ተከስተዋል:: ይህ የሆነው ግን በሐዋርያት ቀጥተኛ አገልግሎት ነው:: በሐዋርያት ሥራ ሁሉም ጋ የማይለወጥ ሆኖ የምናገኘው አማኝ ሕይወቱ ይለወጥና ምስክር ይሆን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ ነው:: በሐዋርያት ሥራ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የማናገኘው ግን መንፈስ ቅዱስ ለየት ባሉ መገለጫዎች የመገለጡን ነገር ነው:: ይህም ሆኖ ግን፣ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት ወንጌልን ለተለያዩ ቋንቋዎች ስናደርስ ዛሬም ቢሆን ለየት ያለ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እየተከሰተ ለምስክርነት በተለያዩ ቋንቋዎች ሊያናግረን ይገባል ብለው ማሰባቸው ነው:: ጤናማነት ያላቸው ክርስቲያኖች በመጀመሪያው ክፍለ አመንና በእኛ ዘመን መካከል ያልቀጠሉ ነገሮችን መለየት ሲያቅታቸው፣ የሐዋርያት ሥራን አስተምህሮዎች አግባብነት በሌለው መንገድ በተደጋጋሚ ለማዛመድ ይሞክራሉ::

## የተለያዩ ሁኔታዎች

የሐዋርያት ሥራ ቀደምት ተደራሲያን ከሆኑት ጋር በተለያየ ዘመን ከመኖራችን ባሻገር፣ የተለያ ሁኔታዎች ማለትም የተለያዩ ባህሎች እና ግለሰባዊ ሁኔታዎች አሉ:: በሐዋርያት ሥራ የሚገኙ ሁሉም ተግባራት የተከናወኑት በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት በነበሩ ታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነው:: ስለዚህም፣ የሉቃስ ዘገባ በርካታ ገፅታዎች ከእነዚህ ታሪካዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ጋር የተቆራኙ ናቸው::

አለመታደል ሆኖ፣ ለሐዋርያት ሥራ ትምህርቶች እውነተኛ ሆኖ ለመታየት በሚደረግ ጥረት፣ በየዘመናቱ የነበሩ ክርስቲያናዊ ቡድኖች በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ወደ ነበረችው ቤተክርስቲያን ባህላዊ ልምምዶች ለመመለስ ይሞክራሉ:: ለምሳሌ፣ በሐሥ 5፡42 ውስጥ ቤተክርስቲያን በግለሰቦች ቤት ውስጥ ትሰበሰብ እንደ ነበር እናነባለን:: ይህንንም መሠረት በማድረግ አንዳንድ ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን መሰብሰብ

ያለባት በህንፃዎች ውስጥ ሳይሆን ቤት ለቤት ነው ይላሉ፡፡ በሐሥ 6፡1 ደግሞ፣ በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስቲያን ለመበለቶች ቀለብ ትሰፍር እንደነበር እናገኛለን፡፡ ጥቂት ክርስቲያኖችም እያንዳንዷ ቤተክርስቲያን ዛሬም የመበለቶችን አገልግሎት የአገልግሎቷ ክፍል ልታደርግ ይገባታል ይላሉ፡፡ እርግጥም፣ በዚህ ዘመን የምትገኘው ቤተክርስቲያን በቤቶች ውስጥ ብትሰበሰብ ወይም መበለቶችን ብትመግብ ምንም ስህተት የለበትም፡፡ ሆኖም እነዚህ ልምምዶች በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ ስደት ቤት ለቤት መሰባሰባቸውን ግዴታ አድርጎት ነበር፡፡ ስደት እናሳ በሆነባቸው ወይም ምንም በሌለባቸው ስፍራዎች፣ ቤተክርስቲያን ቤት ለቤት የመሰባሰብ ግዴታ የለባትም፡፡ የእኛ ሁኔታ ከእነርሱ ጋር የሚመሳሰል እስከሆነ ድረስ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን ተግባራዊ ማድረጉ አግባብነት አለው፡፡ የእኛ ሁኔታ የማይመሳሰል እስከሆነ ድረስ ግን፣ እነዚያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች ተግባራዊ የምናደርገው ለየት ባለ መንገድ ይሆናል፡፡

እንዲያውም፣ በራሱ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንኳን ተመሳሳዮቹ መርሆች በተለያየ መንገድ ተግባራዊ ሲሆኑ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 2፡44-45 ውስጥ፣ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን አባላት ያላቸውን ሁሉ በአንድነት የጋራ እንዳደረጉ ሉቃስ ይጠቅስልናል፡፡ ሆኖም፣ በዚያው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በሐዋርያው ጳውሎስ የተመሠረቱት በርካታ ቤተክርስቲያናት በባለጠጎች ወይም በከተማ ሹሞች ቤት ውስጥ ይሰባሰቡ እንደነበር እናገኛለን፡፡ ይህ ሲሆን ግን የጋራ ኑሮ አልተጠቀሰም፣ የትኛውም ልምምድ አልተኮነነም፡፡ ገና ከጅማሬው፣ ተመሳሳዮቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች ወቅታዊ ለሆነው ሁኔታ አግባብነት ባለው መንገድ ተግባራዊ እንዲደረጉቤተክርስቲያን እውቅና ሰጥታ ነበር፡፡ ሃላፊነት በተሞላበት መንገድ ልናዛምደው የሚገባንን ነገር በቁሙ በመገልበጥ ባዶ ኩረጃ ልናደርገው አይገባንም፡፡

የሐዋርያት ሥራን ስነ-ጽሁፋዊ ባህርይ ከገለጽን፣ በሉቃስ ዘመንና በእኛ መካከል የተቋረጡትን ነገሮች ሰፋ ባለው አስተዋፅዖ ካሳየን፣ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመትና በዘመነኛው ዓለም ያለውን ወሳኝ ቀጣይነት ወደ መመልከቱ ልንሸጋገር ይገባናል፡፡

## የቀጠሉ

በሁለቱም ዘመናት በሚኖሩ ክርስቲያኖች ዘንድ ሳይቋረጡ የቀጠሉትን እንዲህ እናጠቃልላቸዋለን፡፡ አምላካችን ያው ስሉስ አሃዱ አምላክ ነው፣ እርሱም በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስብዕና ውስጥ ይኖራል፤ ግባችንም ተመሳሳይ ነው፣ እርሱም በክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ነው፤ ወንጌላችንም አንድ ነው፣ እርሱም የእኛን እምነት፣ ንስሓ እና መታዘዝ የሚጠይቀው የድነትና የመቤዠት መልእክት ነው፡፡ አስቀድመን በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንደነበሩት ክርስቲያኖች ሁሉ ያንኑ አምላክ የምናመልክ መሆኑን እንመልከት፡፡

### ያው አምላክ/አንድ አምላክ

እኛ ዛሬ የምናገለግለውና የምንመሰክርለት አምላክ ሐዋርያትና የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ያገለገሉትንና የመሰከሩለትን አንዱን ጌታ ኢሱስ ክርስቶስን መሆኑን የሉቃስ ዘገባ ያሳስበናል፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን በነበረው በዚያው መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ይታጠቃል፡፡ ሁሉን የምናደርገውም አንዱን አባት ለማክበር ነው፡፡ የእኛ ስሉስ አሃዱ አምላክ አልተለወጠም፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እግዚአብሔር በወንጌል አማካይነት አስደናቂ ሥራ ሠርቷል፣ ዛሬም ያንኑ መሥራቱን ቀጥሏል፡፡ እግዚአብሔር ከግል ሕይወትህ ወይም ከቤተክርስቲያንህ ወይም ከቤተ እምነትህ ሩቅ የሆነ ከመሰለ፣ ነገሮች መሆን እንደሚገባቸው አይሆኑም፡፡ እግዚአብሔር ሲሠራ፣ ለጠፉትን መዳንን

በማምጣት ቤተክርስቲያኑን ሲገነባ ካላየን፣ በንስሓና በእምነት ወደ እግዚአብሔር ልንመለስ፣ በሕይወታችንና በቤተክርስቲያኖቻችን የማዳኑን የጸጋ ሥራ ታሪክ እንዲቀጥል ልንለምነው ይገባናል፡፡

የምናመልከው ያው አምላክ ከመሆኑ ባሻገር፣ በሐዋርያት ሥራ የምናገኛት ቤተክርስቲያን የነበራት ግብ የዛሬዎቹም ክርስቲያኖች ያው ግብ አላቸው፡፡

## ተመሳሳይ ግብ

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ዓላማ በሐዋርያት አማካይነት በክርስቶስ የሆነውን መንግሥቱን መገንባት ነበር፡፡ ቤተክርስቲያንን በልዩ ልዩ መንገድ በማነጽና በወንጌል አማካይነት የቤተክርስቲያንን ድንበር በማስፋት ወደዚያ ግብ ይገሰግሱ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት መላውን ዓለም እንዲሞላ የማድረጉ ሥራ ግን ዐሥራ-ሁለት ሰዎች ብቻ ለጥቂት ዓመታት የሚሠሩት እንዳልሆነም ያውቁ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ ከእነርሱም ህልፈት በኋላ ይህንኑ ሥራ እንድትቀጥል ቤተክርስቲያንን ያዘጋጁ ነበር፡፡ ኢየሱስ መንግሥቱን የመመሥረቱን ሥራ ለሐዋርያቱ እንደሰጠ ሁሉ፣ ሐዋርያቱ ደግሞ ይህንኑ ሥራ ለቤተክርስቲያን ሰጥተዋል፡፡

እርግጥ ነው፣ መንግሥቱን የመገንባቱ ሥራ ኢየሱስ በክብር ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ አይጠናቀቅም፡፡ ስለዚህ፣ የዘመናችን ቤተክርስቲያን ግብም በክርስቶስ መንግሥቱን ከመመሥረቱ የእግዚአብሔር ተልዕኮ ጋር መጣጣም እና ዓለም በጠቅላላ ደግሞም ሕይወትን ሁሉ በእርሱ ጌትነት ስር ማምጣት ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ አንዱ ተቀዳሚ ተግባር ስለ ድነት፣ ሥነ-ምግባር፣ እግዚአብሔርን የመምሰል ባህርይ፣ግንኑነቶች፣ የወንጌል ተልዕኮ እና ስለ ሕይወት አጠቃላይ ጉዳዮች ሐዋርያት ባስተማሩት ትምህርት መደገፍ ነው፡፡ ክርስቶስን የምናከብርና የምንታዘዝ ከሆነ፣ ቤተክርስቲያን እርሱ ሥልጣን ለሰጣቸው ሐዋርያት ልትገዛ ይገባታል፡፡

ለምሳሌ፣ ሉቃስ ሐዋርያት ድንበር ተሻጋሪ በሆነ ባህልና ሁኔታ መንግሥቱን ሲያሰፉ የሄዱባቸውን የተለያዩ መንገዶች ሲዘግብ ጥንቃቄ አድርጓል፡፡ እኛም ፈለጋቸውን በመከተል፣ በዘመናችን መንግሥቱን የማስፋን ግብ ለመምታት ተመሳሳይ መንገዶችን መጠቀም እንችላለን፡፡ አዎን፣ በእኛ ዘመን በቀጥታ ካልቀጠሉት አንፃር አውዳዊ ተዛምዶ ማድረግ ይገባናል፡፡ ሆኖም ከእኛ አጀንዳ ይልቅ ለተገለጠው የእግዚአብሔር ተልዕኮ ራሳችንን ማስገዛት የምንሻ ከሆነ፣ ከበስተጀርባው ያሉት ግቦችና መርሆች በየትኛውም ትውልድ ተመሳሳይ ሆነው ይዘልቃሉ፡፡

በመጨረሻ፣ ያው አምላክና ያው ግብ ያለን ከመሆኑ ባሻገር፣ የዘመናችን ክርስቲያኖችም በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበረችው ቤተክርስቲያን ታደርግ እንደነበረው ያንኑ ወንጌል ለመስበክ ተጠርተዋል፡፡

## ተመሳሳይ ወንጌል

ዓለም የቱንም ያህል ትለወጥ፣ የሰው ዘር በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ በኃጢአት በማመፃቸው ምክንያት የወደቀ፣ ከእርሱም የተለዩና መቤዠት የሚያስፈልጋቸው መሆኑ ሳይለወጥ ዘልቋል፡፡ እኛ ሁላችን ተመሳሳዩ ድነት ያስፈልገናል፡፡ ያም ድነት የተገኘው፣ ኃጢአታችንን ይቅር ባለውና ወደ መንግሥቱ ባፈለሰን፣ በክርስቶስ ነው፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ሐዋርያት ያስተማሩት ይኸው ተመሳሳይ የወንጌል መልእክት ነው፡፡ ሉቃስም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያወጀውን ይህንኑ ወንጌል ነው፡፡ ዛሬም እኛ አጥብቀን ልንይዘውና ራሳችንን ልናስገዛለት የሚገባው ያንኑ ወንጌል ነው፡፡

መልእክቱም እጅግ ቀላል ነው፡፡ በሐሥ 16፡31 ጳውሎስና ሲላስ ለፊልጵስዩስ የወህኒ ጠባቂ እንደነገሩት፣ ወንጌል ይህ ነው፡

*በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት። (ሐሥ 16፡31)*

ይህ ቀላል መልእክት ጽኑ እንድምታ አለው፡፡ የግልና የጋራ ህይወታችንን ገፅታዎች ሁሉ ያካትታል፣ እንድንለወጥ ይሞግተናል፣ለዓለምም የወንጌል ምስክሮች እንድንሆን ያደርገናል፡፡

ይህ ወንጌል ለሁሉም ህዝብ፣ በሁሉም ስፍራ እና በየትኛውም ዘመን ሳይለወጥ ያው ሆኖ ይዘልቃል፡፡ ሁሉም ህዝብ በኃጢአት ከተሞላው የአመፅ ድርጊቱ እንዲመለስና በክርስቶስ እንዲታመን ተጠርቷል፡፡ ሁሉም ህዝብ ለእርሱ ጌትነት ሊገዛ እና መንግሥቱን ሊገነባ ይገባል፡፡ ይህም ጥሪ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ይታወጅ እንደነበረው ሁሉ በእኛ ዘመን ወደሚኖር ወደ እያንዳንዱ ሰው ሊደርስ ይገባል፡፡ ይህ እንዲታዘዙ የሚቀርብ ጥሪ ለአይሁድም ለአህዛብም፣ ለባለጠጋውም ለድሃውም፣ ለወንዱም ለሴቱም ደግሞም ለከበረውም ለተናቀውም ሁሉ ነው፡፡ ቃሉ ለእግዚአብሔር ክብር፣በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚነገር የንጉሡ የክርስቶስ ቃል ስለሆነ፣ የትኛውንም ተቃውሞና እንቅፋት ሁሉ ድል ይነሳል፡፡ የሐዋርያት ሥራ እንደሚያስተምረን፣ የትኛውም ፈተና፣ ውጥረትም ሆነ ተቃውሞ የመቤዠትን እድገትና መስፋፋት ሊገታ የሚችልበት ኃይል የለውም፡፡ የዘመናችን ክርስቲያኖች ሐዋርያት ሲሰብኩት የነበረውን ወንጌል ለማወጅ፣ እያንዳንዱን ሰው ወደ ንስሓና በክርስቶስ ወደ ማመን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ታማኝ ዜጎች እንዲሆኑ ለመጥራት ደፋርና ባለሙሉ ሥልጣን ሊሆኑ የሚገባው ለዚህ ነው፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ተጠቀመበትን የአጻጻፍ ስልት፣ የሥራውን ይዘት እና እነዚያን አስተምህሮዎች በእኛ ዘመን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ሊወሰድ የሚገባውን ተገቢ ተቀዳሚ እርምጃ ተመልክተናል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ ያደረግነው ምርመራ፣ በዚህ ዘመን የእርሱን ባለ ሥልጣን ትምህርቶች ለመረዳት፣ ለማድነቅና በእነርሱም አማካይነት ለመኖር የምንችልበትን መንገድ ያመለክተናል፡፡

በብዙ መንገዶች፣ የሐዋርያት ሥራ በክርስቶስ ዘመንና በዘመናችን ቤተክርስቲያን መካከል አገናኝ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የክርስቶስን ስብዕና፣ ሥራውንና ትምህርቶቹን የቀደመችው ቤተክርስቲያን እንዴት ትረዳቸውና ተግባራዊ ታደርጋቸው እንደነበር ያብራራል፣ ደግሞም የዘመናችን ክርስቲያኖች እነዚያኑ ተመሳሳይ ሃሳቦች ሊረዱ እና በሕይወታቸው ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉበትን መንገድ የሚመለከቱ መሠረቶችን ይጥልልናል፡፡ ስለዚህ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተቀመጡትን የሉቃስን ዓላማዎችና ዘዴዎች መገንዘብ በቻልን መጠን፣ ከሞት የተነሣውን ንጉሣችንን ማክበርና ማገልገል በምንችልበት መንገድ እንድንኖር ይበልጥ የታጠቅን እንሆናለን፡፡